# የት ደርሰናል? ከእንግዲህስ ወደየት?

የት ደርሰናል? ከየትስ ተነሳን? ያ ትውልድ ወደ ፖለቲካ መድረኩ ከገባበት ወቅት ጀምሮ ያለውን ጊዜ ስናጤን፣ ትውልዱ በርካታ ሀገራዊ ጥያቄዎች ይዞ ቢነሳም፣ ከጥያቄም በላይ ጥያቄ የሆኑ አራት ጉዳዮች ይገኛሉ፡፡ እነሱም፣ ሀ/ ሀገራዊ ነፃነት፣ ለ/ የመሬት ጥያቄ፣ ሐ/ ሀገራዊ ግንባታና ዲሞክራሲ፣ መ/ የእኩልነት ጥያቄ ናቸው፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ ካገኙ ለሌሎቹ መፍትሄ መሻት የቀለለ ይሆናል፡፡

## ሀ/ የት ደርሰናል? ሀገራዊ ነፃነት

የሀገራዊ ነፃነት ጉዳይ ለተወሰነ ጊዜ ትኩረት ሳይደረግበት የቆየ ቢሆንም፣ ህወሃት በኢትዮጵያ የመከላከያ ሃይል ላይ ጦርነት ከከፈተበት ወቅት አንስቶ የምዕራቡ ዓለም ከፀብ ጫሪው ጎን በመሰለፍ የሀሰትና የይስሙላ የዲሞክራሲ ጥያቄዎችን በማንሳት ኢትዮጵያም ሆነ መንግስቱ ላይ ከፍተኛ ጫና ሲያሳድር ቆይቷል፡፡ ኢትዮጵያን ለማፈራረስ በሕዝቦቿ ላይ ህልቆ መሳፍርት ግፍ ሲሰፍር የቆየውን ኃይል ከመሳሪያ ጀምሮ በሌሎች ጉዳዮችም ረድቷል፡፡ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ለማንኮታኮትና ሕዝቦቿን ለረሃብ ለመዳረግ ማዕቀብና ተመሳሳይ እርምጃዎች ወስዷል፣ ለመውሰድ እየሞከረም ነው፡፡ መንግስቱን አጣብቂኝ ውስጥ በመክተት እንዲንበረከክ ለማድረግ ብዙ እየጣረ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ግን፣ ትናንትና የኢትዮጵያ ሕዝብ አልፈልግህም ብሎ ከሥልጣን ያስወገደውን ህወሃትን መልሶ ወደ ሥልጣን ለማምጣት እየጣረ ነው፡፡ ዛሬም እንደ ትናንቱ የምዕራቡ ኃይል በሀገራዊ ጉዳያችን ውስጥ ጣልቃ በመግባት የበላይነቱን ያሳያል፡፡ እናም፣ የት ደርሰናል ብለን ስንጠይቅ፣ መልሱ የትም አልደረስንም ይሆናል፡፡ ትናንት የያ ትውልድ አባላት፣ የምዕራብ ዓለሙ ተገዢ መሆናችን ይብቃ፣ ነፃ ሀገር፣ ነፃ ዜጋ ብለው ያስተጋቡት ጩኸት መና ሊቀር ነው፡፡ ከእንግዲህ ወደየት መሄድ አለብን ብለን ስንነሳ፣ በአድዋና በአምስቱ አመት የኢጣልያን ጦርነቶች አባቶቻችን ያጎናጸፉንን ክብርና ሞገስ እንደለበስን ለመቆየት፣ ትውልዳችን ጭምር ለነፃነት ያደረገውን ተጋድሎ እንዲቀጥል በጽናት መታገል ተገቢ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነቱን ተገፎ ለባርነት እንዳይዳረግ፣ የመንግስት ኃላፊዎች፣ በግፊትም ሆነ በሌላ ምክንያት ሸብረክ እንዳይሉ አስፈላጊውን ግፊት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በአጭሩ፣ ያ ትውልድ

ከ50 አመት በፊት ያነሳው የሀገራዊ ነፃነት ጥይቄ ዛሬም እውን ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሰማያት በጥቁር ደመና ተሸፍኗልና ልንገፈው ይገባል፡፡

እዚህ ላይ ሊጤን የሚገባው፣ በዓለም ዙሪያ አዲስ ሥርዓት እየተወለደ ነው፡፡ (A new world order is on the rise) የምዕራቡ ዓለም በተለይም የሚጢጢዋ የእንግሊዝ የበላይነት ተገድቦ ሌሎች ኃይሎችም ተገዳዳሪ የሚሆኑበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው፡፡ በተለይም ሩስያና ቻይና፡፡ ይህ አዲሱ የዓለም ሥርዓት፣ ምናልባት በሁለት ልዕለ ኃያላን ብቻ ሳይሆን በሶስት፣ ማለትም፣ በምዕራቡ ዓለም፣ በሩስያና በቻይና መሪነት ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይችላል፡፡

የአንድና የሁለት ልዕለ ኃያላን ሥርዓቶችን አልፈንባቸዋል፡፡ የሶስት ልዕለ ኃያላን (tri-polar) ሥርዓት ምን እንደሚመስልና ምን ይዞ ሊመጣ እንደሚችል ስለማናውቅ መገመት ከባድ ነው፡፡ ለማንኛውም፣ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ስለ ዓዲሱ የዓለም ሥርዓት መወለድ ዝርዝር ጉዳይ ውስጥ መግባት ባይቻልም አንኳር አንኳር ሃሳቦችን ማንሳት ይቻላል፡፡ በተቀዳሚ ግን፣ አርኖልድ ቲዮምቤ የተባለ እንግሊዛዊ የታሪክ ምሁር፣ ፈለስፋና ፀሃፊ፣ ሁሉም ግዛተ-አፄዎች (Empires) ጊዜአቸውን ጠብቀው ይወድቃሉ በማለት፣ የአነ ግሪክን፣ ሮምን፣ ኦቶማን ቱርክንና ሌሎችን ዋቢ በማድርግ ትንበያ መሰል ሃሳብ ሰንዝሮ ነበር፡፡ አሁንስ፣ የአሜሪካ ጊዜ ደርሶ ይሆን?

የመጀመሪያው የዓለም ሥርዓት ከ2ተኛ የዓለም ጦርነት ማብቂያ ጀምሮ እስከ 1980ዎቹ አመታት አጋማሽ አካባቢ ነግሶ ቆየ፡፡ ዓለም በሁለት ልዕለ ሃያላን መዳፍ ስር ወድቃ ለሁለት ተከፈለች፡፡ የበላይነትን ለመጎናጸፍ በመሃከላቸው ሰፊ ትግል አካሄዱ፡፡ ከሁሉም አስፈሪ የነበረው የጦር መሳሪያ የማምረትና የማከማት ፉክክር ሲሆን፣ እጅግ የረቀቁና ዓለምን በቀላሉ ሊያወድሙ የሚችሉ መሳሪያዎች ተመረቱ፡፡ ሁለቱም፣ የየመሳሪያዎቻቸውን ቃታዎች ጨብጠው ዓለምን በፍርሃት ቆፈን ውስጥ ከተው ቆዩ፡፡ ከዚያ ሌላ፣ በሳይንስ፣ በጠፈር ሳይንስ ጭምር፣ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ተጽእኖቸውን በማስፋት ሀገራትን በመቆጣጠር፣ ወዘተ ተሰማሩ፡፡ በዚህ ሂደት ሁኔታዎች የተመቻቹለት የምዕራቡ ዓለም የበላይነት በመጎናጸፉ አቸናፊ ሆኖ ወጣ፡፡ ዓለም በአንድ ልዕለ ኃያል ስር ወደቀች፡፡ የሶቭየት ሕብረትም ተበታትና ሩስያ ብቻ አርማውን ይዛ ቀጠለች፡፡

አዲሱ ሁኔታን ተገን በማድረግ የምዕራቡ ኃይል የዓለምን ኢኮኖሚ ለመቆጣጠር ሙከራ ጀመረ፡፡ ሂደቱም ግሎባላይዜሽን ተባለ፡፡ ዋርሶው ፓክት የተባለው የምስራቁ ዓለም ወታደራዊ ተቋም ሲፈርስ የምዕራቡ ዓለም ኔቶ (North Atlantic Tready Organization) ተሰፋፋ፡፡ በርካታ ሀገሮች ተቀላቀሉት፡፡ ዩክሬይንን ጨምሮ፣ የቀድሞ የሶቭየት ሕብረት ደጋፊ የነበሩ ከምእራቡ ዓለም ጋር ሽርክና ፈጠሩ፡፡ አሻፈረን ያሉትም አደጋ ደረሰባቸው፡፡ ዩጎዝላቪያ አንዷ ስትሆን፣ አንድነቷን ጠብቃ ለመቀጠል ብትፈልግም ጫና ተደርጎባት 6-7 ቦታዎች ተፈረካከሰች፡፡ ቬኒዝዌላንና ኩዩባን ለማፍረስ ተሞከረ፣ አልሆነም፡፡ ቻይናን ለማፈራረስ እአአ በ1989 ዓም ቴንአንሜን ስክዌር ላይ እጅግ ትልቅ ሰለፍ በማካሄድ እርምጃው ተጀመረ፡፡ ሁኔታው ወደየት ሊሄድ እንደሚችል የገባው የቻይና መንግስት መጠነ ሰፊ የጉልበት እርምጃ በመውሰድ ንቅናቄውን በአጭር በመግታቱ ዛሬ ቻይና የደረሰችበት ደረሰች፡፡ ለዚህ የቻይና እድገት በርካታ ሁኔታዎች የረዱ ቢሆንም፣ በዋናነት ከሚጠቀሱት መሀል፣ እአአ በ1978 ዓም በዚያን ጊዜ በዋነኛ መሪነት ይቆጠሩ የነበሩት ዴንግ ሲያዎ ፒንግ ያነሷቸው ሁለት መሪ ሃሳቦችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው፣ አርሶ አደሮች ያፈሩትን ምርት ሙሉ በሙሉ መንግስት በተመነው ዋጋ በመንግስት ለሚመሩ ሱቆች በመሸጥ ፈንታ፣ ገሚሱን በነፃ ገበያ እንዲሸጡ መፈቀዱ ሲሆን፣ ይህም አርሶ አደሮቹ ወረት፣ ካፒታል፣ እንዲያጠራቅሙ በመርዳቱ በቀላሉ ለማደግና ለመስፋፋት ቻሉ፡፡ ያ ትንሽ የሚባል ፖሊሲም ቻይና ዛሬ ለደረሰችበት የእድገት ደረጃ አንዱ ታሳቢ ሆነ፡፡ ሌላው ከላይ የተጠቀሱት የእኚህ መሪ ሃሳብ “ድመት ጥቁር ትሁን ነጭ አይጥ እስከያዘች ድረስ ምን ችግር አለው” ያሉት ሲሆን፣ ይህ የአነጋገር ዘይቤ፣ (parable) ሲተረጎም፣ ቻይና መበልጸግ ከቻለች፣ ካፒታሊዝምንም ይሁን ሶሺያሊዝምን ልትገለገል ትቻላለች ማለት ነው፡፡

የምዕራቡ ዓለምና የሶቭየት ወራሽ የነበረችው ሩስያ እሰጥ አገባ ውስጥ በነበሩት ጊዜ፣ ቻይና ድምጽዋን አጥፍታ ስራዋን ቀጠለች፡፡ እጇን ፖለቲካ ውስጥ ሳታስገባ፣ ለታዳጊ አገሮች ሸቀጣ ሸቀጥ አቅራቢ፣ ብድር አበዳሪ፣ እንደ መንገድና የባቡር ሃዲዶች የመሳሰሉ የመሰረተ ልማት አውታሮች ገንቢ ሆነች፡፡ ይህ አካሄድ በአንድ በኩል ለቻይና የወረት መከማቸት (capital accumulation) የረዳ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ እርዳታ ተቀባይ ከሆኑ አገራት ጋርም መልካም ግንኙነት እንዲፈጠር ረዳ፡፡ በዚህ ሂደት፣ ከ72 አመት፣ ማለትም እአአ በ1949 ዓም የተፈጠረው መንግስት ቻይናን ዛሬ ከልዕለ ሃይላን መንግስታት ተርታ እንድትሰለፍ አደረገ፡፡

በሌላ በኩል፣ የሶቭየት ወራሽ የነበረችው ሩስያም አርፋ ስላልተቀመጠች፣ ወቅቱን ጠብቃ፣ የምዕራቡ ዓለም አሻንጉሊት ናት ባለችው በዩክሬን ላይ ወታደራዊ ዘመቻ ከፍተች፡፡ ይህ የሩስያ እርምጃ፣ ከሶቭየት ጉያ ወጥተው የምዕራቡ ዓለምን ሙጥኝ ያሉትን ከማስፈራራቱም ሌላ፣ በአውሮፓና በእስያ ውስጥ ሌላ የኃይል አሰላለፍ መፈጠሩን አመላከተ፡፡

በ2022 ዓም፣ ኡክሬንን ተንተርሶና ሰበብ አድርጎ በሶስቱ ልዕለ ኃያላን መሀከል ሲካሄድ የነበረው መሳሳብ ላልቶና ሳስቶ ቋጠሮው ሊበጠስና አዲስ ሥርዓት ሊወለድ በመሆኑ ዓለም ምጥ ላይ ወድቃለች፡፡ እናም፣ ይህ አዲስ ሥርዓት ለዓለም ምን ይዞ ሊመጣ ይችላል ብሎ ትንበያ አዘል አጠቃላይ አስተያየት መስጠት ቢቻልም፣ ጉዳዩ ሰፊ፣ ገና ያልተቋጨና ብዙ የማናውቃቸው ፋይዳዎች ስለሚገኙ ሙሉ ስዕሉን ማሳየት አይቻልም፡፡

ለማንኛውም ግን፣ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ፣ የመጀመሪያና ተቀዳሚ ስራው፣ በሶስቱ ልዕለ ኃያላን መሀል ያለውን አንድነትና ልዩነት ማወቅ ነው፡፡ ትናንት ኢትዮጵያ ስትከተለው የነበረው የውጭ ፖሊሲ ጊዜ እየከዳው መሄዱን በመረዳት፣ መጪውን የአዲሱ ዓለም ሥርዓትን የሚመጥን ጠንካራ ፖሊሲና አቅጣጫ መንደፍ ተገቢ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሚከተሉት እውነታዎችን ያጤነ ሊሆን ይገባዋል፣

- *ኢትዮጵያ ከምስራቁ ዓለም በተለይም ከሩስያና ከቻይና ጋር እያጠናከረች የሄደችውን ግንኙነት የምዕራቡ ዓለም በግዴለሽነት እንደማይመለከተው፣*
- *ቻይና ከፉኛ መመንደጓ ያሳሰበው የአሜሪካ መንግስት፣ ችግሩን ለመቋቋም የተለያዩ መላዎች እንደሚፈልግ፣ አንደኛው ዘዴም ጀርመንና ጃፓን በአፍሪቃ ውስጥ ጎላ ያለ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ማሳሰብና መጎትጎት እንደሆነ፣*
- *የኤደን ባህረ ሠላጤ፣ ወይም በአረብኛው ከባብ ኤል መንደብ ጋር የተያያዘው ሲሆን፣ በሜዲተራንያን ባህር አድርጎ፣ ቀይ ባህርን አቋርጦ ሕንድ ውቅያኖስ የሚገባው የባህር ላይ የንግድ መስመር ጠቃሚነቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሄዱን፣*
- *ይህ ቀጭን ባህረ ሠላጤ፣ በአንድ በኩል በአረብ ባህረ ገብ መሬት (Arabian Peninsula)፣ በሌላ ደግሞ በአፍሪቃ ቀንድ መሀል ይገኛል፡፡ ባህረ ሠላጤውም ሆነ አካባቢው የተለየ ትኩረት ያገኘው ሽፍቶች መርከብ በማስቆም በገንዘብ መደራደር ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ ሲሆን፣ በርካታ ግዙፍና ሀብታም አገሮች ትኩረታቸውን ጥለውበታል፡፡ ዋና ዋናዎቹ፣ ቻይና፣ አሜሪካ፣ ሩስያ፣ ሳውዲ አረቢያ፣ ቱርክ፣ ኢራን፣ ኤሚሬቶችና*

ሌሎች የአረብ አገሮች ናቸው፡፡ ይህ ቀጠና ከፍተኛ ርኩቻ፣ ፉክክርና ትንቅንቅ የሚካሄድበት ከባቢ ሲሆን፣ የቻይና እና የአሜሪካ ጉዳይ ጎልቶ ይታያል፡፡ የአረብ አገሮቹ ዋነኛ ትኩረት፣ የመሰረተ ግንባታ፣ ሪል ኤስቴት፣ እርሻና ሌሎች ግንባታ ነክ የሆኑ የኢኮኖሚና ጂኦፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ሲሆን፣ ቻይና እና አሜሪካ፣ ከኢኮኖሚ በዘለለ ወታደራዊና ሌሎች ጉዳዮች ላይ አተኩረዋል፡፡
ወደአካባቢው በመጡ አገራት መሀል ፉክክሩና ፍትጊያው እየጠነከረ በመሄዱ፣ የወታደራዊ የጦር ሰፈሮችና የባህር ሃይል ግንባታው እየተጧጧፈ ሂዷል፣

- ጅቡቲና ኢትዮጵያ ባደረጉት ስምምነት፣ ኢትዮጵያ የምታመርተው የተፈጥሮ ጋዝ፣ በቻይና ኩባንያ በሚገነባውና ቀይ ባህር ላይ በሚገኘው የጅቡቲ ወደብ በኩል እንዲከፋፈል ስምምነት መደረጉን፣
- እናም፣ ኢትዮጵያና ቻይና በጣም እየተቀራረቡ መሄዳቸው የምዕራቡ ዓለምን አስደንገጧል፡፡ ኢትዮጵያ ከቻይና በወሰደችው ብድር ብዛት ከጅቡቲ ቀጥላ ሁለተኛ ስትሆን፣ የገንዘቡ መጠንም በብዙ ቢልዮን ዶላር ይቆጠራል፡፡ ከ200 ሚልዮን ዶላር በላይ የፈጀው የአፍሪቃ ህብረት ህንፃ አዲስ አበባ ነው የሚገኘው፡፡ የቻይና የንግድ ሚኒስቴር ወኪል፣ ቻይና ለአፍሪቃ የምትሰጠውን ፈንድ የሚከታተለውና ሺንዋ የተባለው የቻይና የቀጠናው የዜና ወኪል ቢሮዎች አዲስ አበባ ናቸው፡፡ በመገንባት ላይ ያሉት የኢትዮ-ጅቡቲ የባቡር ሀዲድና የውሃ ቧንባ እንዲሁም 500 ሚልዮን ዶላር አካባቢ ያወጣው የአዲስ አበባ የባቡር መስመር፣ የቀለበት መንገዱ፣ የቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ በቻይና ነው የተገነቡት/የሚገነቡት፡፡በቻይና የገንዘብ እርዳታ ጭምር የተገነባው የምርምር ሳተላይት፣ ሻንሲ በተባለ የቻይና ክፍለ ሀገር ነው የሚገኘው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የህዳሴ ግድቡ ስራ እንዲቀላጠፍ በማሰብ፣ የቻይና ኩባንያ በተቋራጭነት እንዲሰራ ተደርጓል፡፡
- ከላይ የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖ፣ እአአ በ2017 ዓም ጅቡቲ ላይ ቻይና የወታደራዊ አምባ ስትመሰርት ነበር አሜሪካ ክፉኛ የባነነችው፡፡ የሁለቱ አገሮች ወታደራዊ የጦር ሰፈሮች አጠገብ ለአጠገብ መገንባታቸው "ትልቅ ተግዳሮት" ነው አሉ በጅቡቲ የአሜሪካ አምባሳደር፡፡ ጅቡቲ ከቻይና ጋር ያደረገችው ሽርክና "የአሜሪካን እንደልብ መንቀሳቀስና ተሰሚነት ያኮስሳል" ሲሉ በአፍሪቃ የአሜሪካ ወታደራዊ ኃይል መሪ ለአሜሪካ ኮንግረስ ተናገሩ፡፡ ከጥቂት አመታት በፊት ልዑክ መርተው ጅቡቲ የሄዱት ሴኔተር ኢንሆፌም ደስተኛ አለመሆናቸውን አሳወቁ፡፡

ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎች በቻይና እና በኢትዮጵያ መሀል የሚደረጉ መቀራረቦች ናቸው የአሜሪካን መንግስት ሊያስከፉ የቻሉትና

*የጠ/ሚኒስቴር ዓብይ መንግስትን በጥርጣሬ ዓይን እንዲታዩ ያደረጉት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፣*

- *ሱማሌ፣ ሱማሌላንድ፣ ጅቡቲ፣ ኤርትራና ኢትዮጵያን ጨምሮ "የአፍሪቃ ቀንድን፣ የአፍሪቃ ክንድ" እናደርጋለን የሚለው የጠ/ሚኒስቴር ዓብይ ራዕይ ስራ ላይ ከዋለና የጋራ ፖሊሲ መንደፍ ከተቻለ፣*
  - *የሕዝብ ቁጥሩ ወደ 150 ሚልይን የሚጠጋው ይህ ቀይ ባህርና የሕንድ ውቅያኖስ ላይ የሚገኘው አካባቢ፣ ትልቅ ገበያ ሊሆን ከመቻሉ በላይ፣ በየብስም ሆነ በባህር ላይ በርካታ የልማት ስራዎች ሊከናውን ይችላል፣*
  - *በአንድነት የተሰባሰቡት እነዚህ አገራት ጠንካራ የወታደራዊና የባህር ሃይል ለመመስረትና ለማስተዳደር ጉልበቱም አቅሙም ይኖራቸዋል፣*
    *ከህዝብ ቁጥር ባለፈ፣ በኢኮኖሚ ሊጎለብቱ ከቻሉ ነፃነታቸውን፣ ልዑላዊነታቸውንና ክብራቸውን ያስከብራሉ፤ ጥቅማቸውን ያስጠብቃሉ፣*
  - *አካባቢው የጦርነት ሳይሆን ወደ ሰላም ቀጠናነት ሊቀየር ይችላል፡፡*
  - *ለአህጉሩ ተምሳሊተ በመሆን፣ ሌሎችም ተመሳሳይ እርምጃ ሊወስዱ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎች ትሩፋቶች የኃያላኑን ጥቅሞች የሚጋፉ በመሆናቸው በበጎ ዓይን የሚታዩ አይደሉም፣ (በሰኔ ወር 2013 ዓም፣ በፍትህ መጽሄት ላይ ባወጣሁት መጣጥፍ ላይ ተመስርቶ የተሰራ)*

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱ ማስረጃዎች ሁኔታው ውስብስብ መሆኑን የሚያመላክቱና የብዙ አዋቂዎችን ምክር የሚጠይቅ በመሆኑ፣ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዓብይ፣ ብልህና ልምድ ያካበቱ ዜጎችን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ አማካሪ አድርገው ሊያሰማሩ ይገባል፡፡ አለበለዚያ ሀገሪቱ የከፋ ችግር ውስጥ ትወድቃለች፡፡

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅቶችም፣ ኢህአፓም ጭምር፣ አዲሱ ሁኔታን በመረዳት ፖሊሲ መንደፍና አዲስ የግንኙነት መስመር ለመፍጠር መሞከር ይኖርባቸዋል፡፡

ዛሬ፣ የምዕራቡ ዓለም በኢትዮጵያ ላይ ዘርፈ-ብዙ እርምጃዎች ለመውሰድ የሚሞክረው በከፊል ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች እንደሆነ መገመት ይቻላል፡፡ እርምጃዎቹ አንድም በራሱ በአሜሪካ፣ ሌላው ደግሞ በተባበሩት መንግስታት

አማካይነት ነው፡፡ ህወሃት በኢትዮጵያ ላይ መዓት ያዘንብ በነበረበት ጊዜ ዝምታን የመረጠው ብሎም በወንጀሉ ይሳተፍ ለነበረው ቡድን ግልጽ ድጋፍ ይቸር የነበረው የምዕራቡ ዓለም፣ ዛሬ ለኢትዮጵያ ህዝብ ተቆርቋሪ መስሎ ቢቀርብ የአዞ እንባ እንጅ ሌላ አይደለም፡፡ መቼም ሆነ መቼ፣ የምዕራቡ ዓለም ተቀዳሚ ጥያቄ የራሱን ጥቅምና ፍላጎት ማሳካት መሆኑን በርካታ አብነቶች መጥቀስ ይቻላል፡፡ ዝርዝር ውስጥ ሳልገባ የአሁኑ የምዕራቡ ዓለም አካሄድ፣ አመራሩን በማንበርከክ ህወሃትን ወደ ሥልጣን ለማምጣት መሆኑን መሳት አያስፈልግም፡፡

በሀገራችን የሰፈነውን የቅራኔ አሰላለፍ ስንተነትንና ኢትዮጵያ በአዲሱ የዓለም ዙሪያ ሊኖራትና ልትይዝ የሚገባውን አቋም ስንመለከት፣ የምዕራቡ ዓለም መሳሪያ የሆነው የተባበሩት መንግስታት ኢትዮጵያ ላይ ሊጥልና ሊያሳልፍ የሚፈልጋቸውን እርምጃዎች መረዳት ቀዳሚ ጉዳይ ነው፡፡

በትግራይ ተፈጸመ የተባለውን የሰብአዊ መብት ጥሰት ለማጣራት ከጥቂት ወራት በፊት የተባበሩት መንግስታትና የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት አካል ሰፊ ፍተሻና ክትትል አድርገው ያ ችግር አለመፈጸሙን የሚያሳይ ዘገባ ቢያቀርቡም የምዕራቡ ዓለም ሳይቀበለው ቀረ፡፡ እናም፣ ይህንኑ ጉዳይ በተመለከተ ራሱ አሜሪካ ኤች አር 6600 የሚባልና ሌላ እቅድ ነድፎ ከጋምቢያና ከኬንያ የመረጣቸውን ሁለት ደጋፊዎቹን በመያዝ የማጣራት ስራ ሊያካሂድ ይፈልጋል፡፡ ማጣራቱ ባልከፋ፣ የሚያስገርመው ግን፣ ጋሪውን ከፈረሱ እንዲሉ፣ ገና ክትትሉ ሳይካሄድ በኢትዮጵያና አንድ 20 በሚሆኑ መሪዎች ላይ እቀባ እንደሚደረግ ለመወሰን ጥረት መደረጉ ነው፡፡ የዓለም ባንክ፣ አይ ኤም ኤፍ፣ እና ሌሎች 12 የገንዘብ ተቋማት፣ የአውሮፓ ህብረት፣ ኔቶ፣ እንግሊዝና ሌሎችን የእቀባው ተባባሪዎች ለማድረግ እየተሞከረ ነው፡፡ ዕቀባው ስራ ላይ ከዋለ መሪዎቹን ሊጎዳ ይችላል፣ በዋነኛነት ግን ኢትዮጵያን ነው ችግር ላይ ሊጥል የሚችለው፡፡ ከጥቂት ወራት በፊት አገዋ የተባለው የአሜሪካ ፖሊሲ በኢትዮጵያ እንዳይሰራ ሲደረግ፣ በአንድ ቅጽበት ስንት ድሆች ለስራ አጥነት መዳረጋቸውን ማጤን ተገቢ ነው፡፡

የምዕራቡ ዓለም እውነት ለኢትዮጵያ የሚቆረቆር ቢሆን፣ ህወሃት በአማራ ክልልና በአፋር ያካሄዳቸውን ከፍተኛ እልቂትና ውድመት አውግዞ ድርጅቱን በዘር ማጥፋት ወንጀልም ሆነ በሌላ በከሰሰ ነበር፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት፣ በተለይም የኦሮምያ ክልል፣ የዘር ክስ ሊቀርብበት ከቻለ በወለጋና በሌሎች ቦታዎች ቆፍረው በሚያድሩ የአማራ ተወላጆች ላይ የተካሄደውና በመካሄድ ላይ ያለው ፍጅትንና ማፈናቀልን ሊያስቆም አለመቻሉና በሚካሄደው ግፍ ተሳታፊ የሆኑ አንዳንድ የመንግስት ሹመኞችን ለፍርድ አለማቅረቡ መሆን ነበረበት፡፡ የአሜሪካ ዋነኛ ፍላጎት ህወሃትን ወደ ሥልጣን ማምጣት በመሆኑ፣ ያ ጉዳይ አያሳስበውም፡፡ አያስጨንቀውም፡፡

ወደ ዋናው ቁም ነገር ስንገባ፣ ዛሬም እንደትናንቱ በመጀመሪያ ደረጃ ሊጠቀስ የሚገባው የምዕራቡ ዓለም የኢትዮጵያን ነፃነት ለመግፈፍ የሚያደርገው ጥረት ዋነኛው ቅራኔ እንደሆነ መረዳት ነው፡፡ በኢትዮጵያና በምዕራቡ ዓለም መሀል እሰጥ አገባው እየተጋጋለ ይሄድ በነበረበት ጊዜ "በቃ" ወይም #no more# በተባለ መሪ ሃሳብ ስር በሺዎችና አስር ሺዎች ተሰልፈው ድምጻቸውን አሰሙ፡ ፡ ይሁንና፣ ይህ ሂደት ይካሄድ በነበረበት ወቅት የህዝቡ ትግልና ስሜት ላይ ቀዝቃዛ ውሃ ተቸለሰ፡፡ በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት የቀሰቀሱ የህወሃት መሪዎችን ሕዝብ ሳያውቅ ከእስር በመፍታታቸው ብዙዎችን አበሳጨ፡፡ ሌሎች ተመሳሳይ እርምጃዎች በመወሰዳቸውም፣ በተለይ በውጭ ሀገራት የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ-ኢትዮጵያውያንን አስቆጣ፡፡ ተቆጥተውም ዝም አላሉም ለዚህ መንግስት ይቸሩ የነበረውን ድጋፍ ነፈጉ፡፡ በቅርቡ፣ HR 6600ንና ሌላውን ፖሊሲ በመቃወም በአሜሪካ በተካሄደው ሰልፍ 150 የሚያህል ሰው ብቻ ሊገኝ የቻለው አንድም መንግስት ተሸሽጎ በሚወስዳቸው እርምጃዎች በመበሳጨቱ መሆኑን መገመት ከባድ አይደለም፡፡

ኢትዮጵያን በሚመሩ አካላት በኩል ተደጋጋሚ ስህተት ይፈጸማል፡፡ ይሁንና፣ ዜጎች አመራሩንና ኢትዮጵያን ነጥለው በማየት፣ በአንድ በኩል ለኢትዮጵያ ጥብቅና መቆማቸውን ሳያቋርጡ፣ በሌላ በኩል በአመራሩ ላይ የሚሰማቸውን ቅሬታ በሕዝባዊ ሰልፍ ጭምር ማሳየት ይኖርባቸዋል፡፡ "በቃ" ወይም #no more# የተባለውና የብዙዎችን ቀልብ ሊገዛ የቻለው መሪ ሃሳብ ህልው እንዲሆን ከተሸጎጠበት ቅርቃር በማውጣት ማሰባሰቢያ መፈክር ሆኖ በመላው ዓለም እንዲናኝ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ በዚህ መሪ መፈክር ዙሪያ ሚልዮኖችን በማሰለፍ ለኢትዮጵያ ነፃነት መቆም ጊዜው የሚጠይቀው ግዳጅ ነው፡፡ ማንም ሆነ ማ፣ ጠቅላይ ሚኒስቴሩም ጭምር፣ በዚህ መሪ ሃሳብ ላይ ቀዝቃዛ ውሃ እንዳይቸልስበት ነቅቶ መጠበቅ የዜጎች ሁሉ ግዴታ ሊሆን ይገባል፡፡

**የመምረጥና የመመረጥ መብት ለትውልደ ኢትዮጵያዊው**

የ“በቃን” መፈክር በማንገብ ትልቅ ሚና የተጫወተው በውጭ ሀገራት የሚገኘው ትውልደ ኢትዮጵያዊው ሲሆን፣ ይህ የህዝብ ወገን ኢትዮጵያን ይበልጥ እንዲያግዝ፣ ግዴታውንና መብቱን ባገናዘበ ሁኔታ በተሻለ መንገድ ሊደራጅ ይገባል፡፡ በአመዛኙ በሁኔታዎች አለመመቻቸት ምክንያት በዓለም ዙሪያ የተበተነው በሚልዮኖች የሚቆጠረው ዜጋ፣ በትውልደ-ኢትዮጵያዊነቱ፣ በዕውቀቱ፣ በልምዱ፣ ከሚኖርባቸው አካባቢዎች ባላው ግንኙነትና ራሱን ችሎና ሀብት አፍርቶ የሚኖር መሆኑን በማገናዘብ ኢትዮጵያ ልታቅፈው ይገባል፡፡ ይህን ማድረግ የሚቻለው ደግሞ፣ ዜጋውን በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ቀጥተኛ ተሳታፊ የሚሆኑበትን መንገድ በመፍጠር ነው፡፡ 1/ በሁኔታዎች በመገደድም ሆነ በሌላ ምክንያት የሌላ አገር ፓስፖርት የያዙ ኢትዮጵያውያን ጥንድ ዜግነት እንዲኖራቸው አስፈላጊውን ህጋዊም ሆነ ሌላ ዝግጅት ማድረግ፣ 2/ ከተቻለ ሁሉም፣ ያ ሊሆን ካልቻለ በውጭ ሀገራት የሚገኙ የኢትዮጵያ ፓስፖርት የያዙ ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያ የምርጫ ፖለቲካ የመሳተፍ መብታቸው እንዲከበር ማድረግ፣ 3/ በውጭ የሚገኘውን ትውልድ ከሀገሩ ጋር ሊያገናኘው የሚችል፣ በመንግስታት በተመደቡ ሳይሆን እዚያ ባለው ሰው ሊመረጥ የሚችል የመማክርት ሸንጎ እንዲቋቋም ማድረግ፣ 4/ ትውልደ ኢትዮጵያውያን በታክስ መልክም ሆነ በሌላ ለኢትዮጵያ ብልጽግና የሚውል ገንዘብ እንዲያወጡ ማድረግ ሲሆን፣ ይህ አሰራር ከመጪው ምርጫ አስቀድሞ ስራ ላይ እንዲውል ማድረግን ይጠይቃል፡፡

## ለ/ የት ደርሰናል? መሬት ለአራሹ

የት ደርሰናል? የሚለውን ጥያቄ በድጋሚ ስናነሳ፣ ከአመታት በፊት ያ ትውልድ ያነሳው የመሬት ጥያቄ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ መመርመር አማራጭ የለውም፡፡

ለመሬት ጥያቄ መፍትሄ መስጠት አስፈላጊ ከሆነበት ምክንያት አንዱ ችጋርን ለመዋጋት ቢሆንም፣ በ1960ዎቹ አመታት ትግራይና ወሎን ብቻ ያካልል የነበረው ችጋር፣ “በ1970 ዓም በኢትዮጵያ በአራት ክፍለ ሃገራት ማለትም በጎንደር፣ ሸዋ፣ ትግራይና ወሎ 1 ሚሊዮን አርባ ሺህ ረሀብተኛ መኖራቸው ተገለጠ። በ1971 ዓም በስድስት ክፍለ ሀገራት ማለትም በኤርትራ፣ ሐረርጌ፣ ሲዳሞ፣ ሸዋ፣ ትግራይና ወሎ የረሀብተኛው ቁጥር 2,800,000 ደረሰ። በ1972 ዓም ረሀብ በሰባት ክፍለ ሀገራት ማለትም በባሌ፣ ኤርትራ፣ ሐረርጌ፣ ሸዋ፣ ሲዳሞ ትግራይና ወሎ ተከስቶ የረሀብተኛው ቁጥር 3,000,000 አለፈ። በ1973 ዓም

በዘጠኝ ክፍለ ሀገራት ማለትም በባሌ፣ ጋሙ ጎፋ፣ ጎንደር፣ ኤርትራ፣ ሐረርጌ፣ ሲዳሞ፣ ሸዋ፣ ትግራይና ወሎ የረሀብተኛው ቁጥር 5,089,000 ደረሰ።" (New Ethiopia: Famine in Ethiopia, July 1980፣ ነገደ ጎበዜ፣ ገጽ 269) በ1977 ዓም ችጋር ድንበር የለሽ ሆነ።

የዛሬው መንግስት ስልጣን በያዘበት በ2010 ዓም አካባቢም፣ ችጋር ዓይኑን አፍጦና አግጦ ኢትዮጵያን ጎበኛት። በ1965ና በ1977 ዓም እንደተፈጸመው፣ ዛሬ በ2014 ዓም በበርካታ የኢትዮጵያ ክባቢዎች ዜጎችና ከብቶቻቸው እየረገፉ ነው፡፡ ለአብነት የሱማሌና የደቡብ ኦሮምያ ክልልን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከሰው ሰራሹ ጦርነት ጋር ተዳብሎም በአማራና በአፋር ክልሎችም ችግሩ ድንበር የለሽ ሆኗል፡፡ የችግሩ አስከፊነትንና ምን ያህል የሰው ልጅ ስብእናን እንደሚፈታተን ለመረዳት፣ "ችጋር ምንም የሚላስ፣ የሚቀመስ በመጥፋቱ ሰዎች በአካላቸው ውስጥ በአከማቹት እየተጠቀሙ ዕለት በዕለት አካላቸውን እየጨረሱ፣ እያወቁት ቀስ በቀስ ወደተረጋገጠ ሞት የሚሄዱበት የኅብረተሰብ በሽታ ነው። ቤተሰብ ይፈርሳል፤ ኅብረተሰብ ይፈርሳል። ባል ለሚስቱ፣ እናት ለልጅዋ፣ ዘመድ ለዘመድ ያለው ፍቅርና ቅን መንፈስ ሁሉ ተንኮታኩቶ እያንዳንዱ ሰው ለብቻው የየራሱን ጻዕር እያብሰለሰለና እያቃሰተ የሚደቀስበት በሽታ ነው። ሕፃን ልጅ የእናቱ ጡት መድረቁን ባለማወቁ እያኘከ የቦጨቃቸውን ጡቶች አይቻለሁ፤ እናቲቱም በባሰ ችጋር ሕመም ተይዛ ከእንደዚህ ዓይነቱ ሕመም ውጭ ነበረች።

"ችጋር የሰው ልጅ እንደማገዶ እንጨት ተለብልቦ የሚያልቅበትና ቀባሪ እንኳን የማያገኝበት የውርደት ሞት ነው፤ የሰው ልጅ ውርደት ነው፤ የኅብረተሰብ ውርደት ነው፤ የአገር ውርደት ነው። ቁራሽ እንጀራ ወይም እፍኝ ቆሎ የሚሰጥ ዘመድ ወይም ወዳጅ ወይም ወገን ጠፍቶ፣ ለነፍሱም ይሁን ለሰብዓዊ ርኅራኄ ተነሳስቶ፣ የሚረዳ ጠፍቶ በሺህና በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች በየቤታቸው፣ በየመንገዱና በየገበያው የሚወድቁበት ሁኔታ ነው።" (ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም፣ ህዳር 2008፣ ከድህረ ገጽ የተገኘ)

የመሬት አዋጅ ከወጣ ከ47 አመታት በኋላም ችጋር አልተወገደም። ደርግ ወድቆ ኢህአዴግ፣ ኢህአዴግ ወድቆ ብልጽግና ቢተካም ችጋር የኢትዮጵያን ምድር ጥሎ አልሄደም። እንዲያውም በየአመቱ ይጎበኛታል! አርሶ አደሩ ለነፃነቱ ያደረገው ትግል በመኮላሸቱ፣ ሥልጣን ላይ የወጣ መንግስት እንዳሻው ይፈነጭበታል። የግብዓት ችግሩም ቀላል አይደለም።

እንደ ሌሎች የአፍሪቃ አገሮች፣ በየጊዜው በኢትዮጵያ ለሚቀሰቀሰው ችጋር፣ የአየር ጠባይ፣ በየአካባቢው የሚነሱ ግጭቶች፣ የግብዐት አቅርቦት፣ ገበያ፣

የሕዝብ ብዛትና የመሳሰሉ ጉዳዮች ቅጽበታዊ ምክንያቶች ተብለው ሊጠቀሱ ቢችሉም፣ አንዱና ዋነኛው ችግር ኢትዮጵያ ለክፉ ጊዜ የምትጠቀምበት በቂ የሆነ የእህል ጎተራ አለመኖሩ ነው። አርሶ አደሩም ቢሆን፣ ለክፉ ጊዜ የሚሆነው እህል አየከማችም። ለምን? በውርስና በመሳሰለው ምክንያት፣ አርሶ አደሩ የሚያርሰው መሬት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያነሰ መሄድ፣ ወጣት አርሶ አደር ቀየውን እየለቀቀ ወደ አቅራቢያ ከተማዎች መሰደድ፣ በመንግስት በኩል እንደጫት፣ አበባና ሩዝ በመሳሰሉ የውጭ ገንዘብ ማስገኚያ ምርቶችና ለውጭ አገራት ፍጆታ ላይ ማተኮርና የመሳሰሉ ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል።

<u>የገጠሩ ነዋሪ ከረሃብና እርዛት ሊላቀቅ የሚችለው፣ የራሱና የአካባቢው ባለቤት መሆን ሲችል ብቻ ነው። በመሬቱ የባለቤትነትም ሆነ የማዘዝ መብቱ ሲከበር ነው። ይህ ደግሞ፣ ትናንት የተጀመረው የመሬት ይዞታ ተሻሽሎና ወደ ገጠር አብዮትነት ተቀይሮ፣</u> የአካባቢው የፖለቲካ ሥልጣን ከጥቂት የመንግስትና የገዢ ፓርቲው ደጋፊዎች እጅ ወጥቶ አርሶ አደሩ እጅ መግባት ሲችል ነው። አርሶ አደሩ፣ በቀጥታም ሆነ ይወክለኛል በሚለው የፖለቲካ ፓርቲ አማካይነት መብቱንና ጥቅማ ጥቅሞቹን ማስጠበቅ የሚችልበት የፖለቲካ ሥርዓት በመዘርጋት፣ ህይወቱንና አካባቢውን የሚቀይርበት ዘዴና ብልሃት ሲያበጅ ነው።

እዚህ ላይ ለታሪክ ማስታወሻነት አንድ ነጥብ ላንሳ፡፡ በ1967 ዓም ደርግ የመሬት አዋጅን ሲያወጣ፣ ለዋነኛ የማታገያ ጥያቄአችን ምላሽ በመስጠቱ የኢህአፓ መርሃ ግብር ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ አሳደረ፡፡ እናም፣ ለዚህና ለሌሎች ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት መለስተኛ ጉባዔ እንዲጠራ ተወሰነ፡፡ የፓርቲው መርሃ ግብርን ለመፈተሽና ረቂቅ ለማዘጋጀት ብቃት አላቸው ተብለው የሚገመቱ አራት አባላት ተመርጠው ስራውን ጀመሩ፡፡ እኔም አመራሩን በመወከል ተሳታፊ ሆንኩ፡፡ ረቂቁን ስናዘጋጅ ከገጠሙን ችግሮች መሀል አንዱ ደርግ ለመሬት ጥያቄ ያቀረበው የመፍትሄ ሃሳብ፣ ማለትም መሬት የመንግስት ነው ሲል መደንገጉ ነበር፡፡ ኢህአፓ በፕሮግራሙ ላይ ያሰፈረው መፍትሄ፣ "መሬት ለአራሹ" የሚል ሲሆን፣ ደርግ ካወጣው አዋጅ ጋር የሚቃረን ባይሆንም የሚጣጣም አልነበረም፣ እናም፣ የደርግ የመፍትሄ ሃሳብ ወቅቱን ያልጠበቀና ለችግር የሚያጋልጥ እንደሆነ ታመነበት፡፡ አርቃቂ ኮሚቴውም መሬት የመንግስት ነው የሚለውን የመፍትሄ ሃሳብ ሊቀበል አልቻለም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፣ ኢህአፓ ያን የደርግ ሃሳብ ተፃሮ ቢወጣ ድርጅቱ በአድሃሪነትና በመሳሰለው ተፈርጆ የፖለቲካ ችግር ውስጥ ሊከተው እንደሚችል ግልጽ ነበር፡ ፡ ምንም እንኳን ጥሩ የመፍትሄ ሃሳብ ነው ባይባልም፣ መሬትን በተመለከተ በሰፈረው የፓርቲው መርሃ ግብር ውስጥ "መሬት የመንግስት ነው" የሚለው

አገላለጽ “መሬት የህብረተሰቡ ነው” በሚል እንዲተካ ተደረገ፡፡ የ1967 ዓም መለስተኛ ጉባዔም ሃሳቡን ተቀበለ፡፡

**ዛሬም ለምን መሬት ለአራሹ**

በኢትዮጵያ፣ የመሬት መቀራመት በሚካሄድበት በአሁኑ ሰዓት፣ አርሶ አደሩ ከአርባ አመት በላይ የያዛት መሬት ለልጅና ለልጅ ልጅ ተሸንሽና ተመናምናለች። ከጥቂት አመታት በፊት የወጣ አሃዝ እንደሚያሳየው፣ “በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ለስራ ከደረሱ 44.7 ሚሊዮን ዜጎች መሀል 32.4 ሚሊዮን፣ ማለትም 72% ስራ አጥ” ናቸው። (የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ የምርጫ ማኒፌስቶ፣ 1997 ዓም ገጽ 45) የአርሶ አደሩ መሬት ለልጆቹ ተሸንሽኖ በመሰጠቱ የሚታረሰው መሬት ምን ያህል እያነሰ እንደሄደ የኢትዮጵያ መንግስት የስታቲስቲክ መስሪያ ቤት ያወጣውን መረጃ እንመልከት።

| ብዛት | ከ .01 (ሄክታር በታች) | ከ.01-.05 ሄክታር | ከ0.51-1.00 ሄክታር | ከ1.01-2.00 ሄክታር | ከ2.01-5.00 ሄክታር | ከ5.01-10 ሄክታር | ከ10 በላይ ሄክታር | ጠቅላላ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የቤተሰብ ብዛት | 1,322,950 | 4,263,558 | 3,723,475 | 3,961,968 | 2,291,980 | 218,017 | 23002 | 15,804,958 |

በኢትዮጵያ የስታቲስቲክ መስሪያ ቤት - እርሻ - ሠንጠረዥ 11-መ

ጠቅላላ የቤተሰብ ብዛት 16 ሚሊዮን አካባቢ ሲሆን፣ በዝቅተኛው ስሌት አንድ ቤተሰብ 4.5 ሰዎችን ይይዛል ብለን ብንገምት፣ የአርሶ አደሮቹ ቁጥር 72 ሚሊዮን ይደርሳል። በሰንጠረዡ መሰረት፣ የበሬ ግንባር ከምታክል ከ.01 ሄክታር (ኩርማን መሬት) ጀምሮ እስከ 2.00 ሄክታር መሬት ያላቸው ደሃ ብለን ልንፈርጃቸው የምንችላቸው ቤተሰቦች ብዛት ከ80% በላይ ሲሆን፣ ከ51 ሚሊዮን በላይ ናቸው ማለት ነው። በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች በመሬት ችግር ተቀፍድደው እያለ በብዙ ሚሊዮን ሄክታር የሚቆጠር መሬት ለውጭ ባለሀብቶች እጅግ ዝቅተኛ በሆነ ዋጋ መስጠት ለአገሪቱ ልማትም ሆነ ለሕዝቡ ኑሮ መሻሻል ምን ያህል ሊጠቅም እንደሚችል መገመት ይከብዳል። ከዚህ በተጨማሪ፣ ከ18 ሚሊዮን በላይ ዜጎች ለችጋር የሚዳረጉበት አንዱና ዋናው ምክንያት በከፊል ከመሬት ማነስና በአጠቃላይም ከመሬት ይዞታ ሥርዓት ጋር በተያያዘ ነው ብሎ መናገር ይቻላል። ስለሆነም፣ በ1966 ዓም

ዕልባት ተበጅቶለታል የተባለው የመሬት ጥያቄ ዛሬም ከሀገሪቱ ዐበይት ጥያቄዎች መሀል አንዱ ሲሆን፣ ንቅናቄው 47 አመታት በላይ ቢያስቆጥርም፣ ዛሬም የብዙ ሚሊዮኖች ጥያቄ ምላሽ አላገኘም። አርሶ አደሩ የመሬት ዋስትና የለውም። የመሬት ባለቤትነት መብቱ አልተከበረም።

እናም፣ መሬት ለአራሹ ሲባል መሬት ለባለቤቱ ማለት ነው፡፡ ይህ ትናንት ሚልዮኖችን ያሰለፈ ጥይቄ ዛሬም አእላፎች ሊሰለፉና ሊዘምሩለት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ ደግሞም ያደርጉታል፡፡ ያ ትውልድ ታሪካዊ ድርሻውን ተወጥቷል፡፡ ይህ ትውልድም የበኩሉን አስተዋጽኦ ማበርከት ይጠበቅበታል፡፡

መሬት ለአራሹ የምንልበት አንዱ ምክንያት አርሶ አደሩን ለመጥቀም ቢሆንም፣ ምክንያቱ እሱ ብቻ አይደለም። መሬት ከፍተኛ ዋጋ ያለው ሀበት ነው፣ ወርቅ ነው። ባለሀብቱ ሊሸጠውና ሊለወጠው ከቻለ። በቢሊዮንና በትሪሊዮን ብር ሊመነዘር የሚችል። ያ ካልሆነ ግን፣ መሬት መሬት ነው። ድንጋይና አፈር። ከአርሶ አደሩ ባለፈ፣ ኢትዮጵያም እምቅ ሀብቷን በአግባቡ ተጠቅማ እድገትና ብልጽግናዋን ማፋጠን መቻል አለባት። በእርግጥ፣ አንድ ቡድን የመሬትን ጥቅም ተረድቷል፡፡ በህወሃትና አሁን ደግሞ በኦህዴድ ዙሪያ የተሰባሰበው አዲሱ የገዢ ቡድን የመሬትን ጥቅም በማወቁ፣ ህገ ወጥ በሆነ መንገድ በብዙ ሚልዮኖች በሚቆጠር ብር እየቸበቸበው ይገኛል። በኢትዮጵያ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ፍትህ እንዲሰፍንና ሙስናን መዋጋት ከተፈለገ የመሬት ባለቤትነት ጥያቄን ከአዲሱ የዘራፊ ቡድን መንጋጋ ፈልቅቆ በመውጣት ለእውነተኛ ባለቤቱ ማስረከብ ያስፈልጋል።

መሬት ለአራሹ የምንለው ገበሬው በንብረቱ ላይ ዋስትና እንዲኖረው ለማድረግና፣ በሀብቱ የማዘዝ ሰብዓዊ መብቱን ለማስከበር ነው። አርሶአደሩ መካሪና መሪ ያስፈልገዋል፣ ሞግዚት ግን አይሻም። ስለ ኑሮው ከራሱ የበለጠ ሊያውቅ የሚችል ማንም አይኖርም። መሬቱን ሲሻው አርሶ ይተዳደርበታል። ከፈለገም፣ ከፊሉን ሸጦ ወይም ወለድ አገድ አስይዞ ያገኘውን ገንዘብ ለፈለገው ተግባር ያውለዋል። መሬትን ወደ ካፒታልነት መቀየር ተገቢ ነው። ያ ሊሆን የሚችለው ደግሞ ዋጋ (value) ሲኖረው ብቻ ነው። የመሬት ሽያጭን በተመለከተ አርሶ አደሩ ውሳኔ ሲያደርግ አይሳሳትም አይባልም። ሊሳሳት ይችላል። ያ ሁኔታ ግን አርሶ አደሩ የመሬት ባለቤት መሆን የለበትም ወደሚል መደምደሚያ አያደርስም።

መሬት ለአራሹ የምንለው አርሶ አደሩ የእኔ የሚለው መሬት ኖሮት በሚገባ ቢያለማው የችጋር አዙሪቱን ለመስበር የሚረዳ መሳሪያና ብልሀት ነው ብለን በማሰብም ጭምር ነው።

*መሬት ለአራሹን የምንደግፈው፣ እየተመናመኑ የሄዱት ደኖቻችንን ለመንከባከብ እንችል ዘንድ ነው። ዛሬ፣ ደኖች እየጠፉ ናቸው። አርሶ አደሩ ዛሬ ወይም ነገ ከመሬቱ ሊነቀል መቻል አለመቻሉን ስለማያውቅ መሬቱን የግሌ ብሎ አይዘውም። አይንከባከበውም።*

*መሬት ለአራሹን የምንደግፈው፣ መሬት ለወጣቱ በማለት፣ ከገጠር የተፈናቀሉና ከተማዎችን ያጣበቡ ወጣቶችም ሆኑ ሌሎች መተዳደሪያ አግኝተው ራሳቸውንና ሀገራቸውን ሊረዱ የሚችሉበት ሁኔታን ለመፍጠር ነው፡፡*

*መሬት ለአራሹ የምንለው መንግስት መሬትን ተገን አድርጎ በአርሶ አደሩም ሆነ በተቀረው ህዝብ ህይወት ውስጥ አድራጊና ፈጣሪ የሆነውን ሚናውን ቢቻል ለመስበር ካልሆነም ለመቀነስ ነው። አርሶ አደሩም ሆነ የተቀረው የህብረተሰብ ክፍል ነፃ ሰው ሊሆን የሚችለው ከመንግስት ጥገኝነት ሲላቀቅ፣ መንግስት በመሬት ላይ ያለው የባለቤትነት ኃይል ሲሰበር ወይም ሲቀነስ ነው።*

*መሬት ለአራሹ የምንለው ከደርግ ዘመን ጀምሮ በመንግስት እርከንና በዙሪያው አዲስ የገዢ ቡድን ስለተፈጠረ፣ እጁ ላይ የወደቀውን እንቁ፣ ማለትም መሬትን፣ በብዙ ሚልዮኖች ብር እየቸበቸበ ነው። በአዲስ አበባ ዙሪያ በየጊዜው የምንሰማቸው፣ "ይህን ያህል መሬት ጠፋ"፣ "ይህን ያህል መሬት ጠፍቶ ነበር ተገኘ"፣ ወዘተ የሚሉት ዘገባዎች ከዚሁ ከመሬት ዝርፊያ ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡*

*መሬት ለአራሹ የምንለው አርሶ አደሩ በዘር ከተከለለው ድንበር በመዝለል ከጎረቤት አቻው ጋር በሚያካሂደው ጣምራ ትግል አማካይነት አንድነቱን በመገንባት ጽንፈኛ ብሄረተኝነት ለመዋጋት የሚያስችል ጠንካራ ኃይል እንዲሆን ለመርዳትም ጭምር ነው፡፡*

*ይህ የመሬት ዝርፊያ ከአዲስ አበባ ባለፈ እንደ ወለጋ በመሳሰሉት ቦታዎች በስፋት እየተካሄደ ነው፡፡ ይህ ሂደት፣ የብልጽግና መንግስት ሥልጣን ከያዘ በኋላ ባሉት ሁለትና ሶስት አመታት ውስጥ ለየት ያለ ገጽታ እየያዘ ሄዷል፡፡ በህወሃት/ኢህአዴግ የመጨረሻ ዘመን የመሬት ቅሚያው ያነጣጠረው በኦሮሞ አርሶ አደሮች ላይ የነበረ ሲሆን፣ በዝርፍያው የተሰማሩት፣ የኢህዴግ አባል ፓርቲዎች አመራሮችና በመንግስቱ መዋቅር ውስጥ የተሰገሰጉ ሸሪኮቻቸው ሲሆኑ፣ አሰራሩም፣ መሬትን ከአርሶ አደሩ በዝቅተኛ ዋጋ በመግዛት መቸብቸብ ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ ይህ ሂደትም ከፍተኛ ቁጣ ቀስቅሶ የቄሮ ንቅናቄን ወለደ፡፡ ከመሬታቸው የተፈናቀሉት የአርሶ አደር አባወራዎች፣ ዛሬ በገዛ መሬታቸው ላይ በዘበኝነት ተቀጥረው ይሰራሉ፡፡ ልጆቻቸው ደግሞ በያለበት ተበትነው የቀን ስራ ተዳዳሪዎች በመሆናቸው፣ አያትና የመሳሰሉ ቦታዎች ጠዋት ላይ ተኮልኩለው ቀጣሪ ሲጠብቁ ያረፍዳሉ፡፡ ይህን በመሰሉ የመሬት ዝርፊያ እጅግ*

በርካታ ወገኖች እንዲደኸዩ የተደረገ ሲሆን፣ የቄሮ ንቅናቄ መነሳት ሂደቱን ገታው፡፡ ሆኖም በመሬት ዘረፋው የተሰማሩ ሃይሎች ስራቸውን አላቆሙም፡፡ ሌላ ሁለት መላዎች ዘየዱ፡፡ የመጀመሪያው መሬት አስገድዶ መቀማት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በኦሮሞዎች ላይ ሳይሆን፣ ትናንት በችጋር ምክንያት ከተወለዱበትና እትብታቸው ከተቀበረበት እርቀው በመሄድ በሰፈሩ "ነፍጠኛ" በሚሏቸው የአማራ አርሶ አደሮች ላይ ሆነ፡፡ ይህን ዝርፊያ ለማሳለጥ፣ የዘር ልዩነትና ጥላቻ ላይ የተመሰረተ ሰፊ ቅስቀሳ ተካሄደ፡፡ በዚህ የዝርፊያ ስራ እስከ ገበሬ ማህበር ድረስ ያሉ የመንግስትና የፓርቲ ሹመኞች የተሳተፉና የሚሳተፉ ሲሆን፣ ተጎጅዎችን መሰረት አድርጎ የተሰራውና በቅርቡ የተለቀቀው "አልሞትኩም ብዬ አልዋሽም" የሚለው የ40 ደቂቃ ሰነዳዊ ፊልም የዝርፊያው ሂደት ምን እንደሚመስል ያሳያል፡፡

እነዚህ የተዘረፉት ወገኖች፣ ከ60-70 በፊት በየቀዬአቸው በደረሰው ከፍተኛ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ችግር፣ በምዕራብና ምስራቅ ወለጋ እንዲሰፍሩ ተደረገ፡፡ ልጆቻቸውም ሆኑ እነሱ ራሳቸው ከአካባቢው ሕዝብና ባህል ጋር ተጋመዱ፡፡ በተለይ ልጆቻቸው ኦሮሞ እንጅ ሌላ ሊባሉ አይችሉም፡፡ ሁኔታው ያ ቢሆንም፣ ዛሬ በተካሄደውና በመካሄድ ላይ ባለው ፍጅት እጅግ ብዙ ዜጎች ተገደሉ፣ ተጎዱ፡፡ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ደግሞ መሬታቸውን፣ ከብቶቻቸውን፣ ቤታቸውንና ሌሎች ንብረቶቻቸውን ተቀምተው ራቁታቸውን ከአካባቢዎቻቸው እንዲሰዱዱ ተደረገ፡፡ ተበተኑ፡፡

ትናንት በኦሮሞዎች፣ ዛሬ ደግሞ በአማሮች ላይ ካነጣጠረው የግፍ እርምጃዎችም ሆነ ከሚካሄደው ዝርፊያ በስተጀርባ ያለው ማነው?

## አዲሱ የገዥ ቡድን

ከ1967 ዓም ጀምሮ በተከታታይ የተወሰዱ የኢኮኖሚ እርምጃዎች፣ በተለየ የገጠር መሬትን በተመለከተ የወጣው አዋጅ፣ በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን የነበሩ የገዢ መደቦችን የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሥልጣን አዳከመ። በ17 አመት የደርግ ዘመን፣ መንግስቱን ከለላ በማድረግ የከበርቴ ቡድን መፈጠር ጀምሮ የ'አየር በአየር' የንግድ ሥርዓት ተዘረጋ። ይሁንና፣ በወቅቱ በነበረው የጦርነት ኢኮኖሚ ምክንያት ቡድኑ ሊጎለብት አልቻለም። በ1983 ዓም ጦርነቱ በመቆሙ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ መንኮታኮቱ ተገታ። ሕወሃት/ኢህአዴግ ሥልጣን ከያዘበት ከዚህ ወቅት ጀምሮ፣ የፖለቲካ ድርጅቶቹን፣ መንግስትን፣ የድርጅቶቹ የኢኮኖሚና የንግድ ተቋማቱንና ወታደራዊ አካላቱን ተገን አድርጎ ተጠቃሚ ኃይል ሊፈጠር የሚችልበት ሁኔታ ተመቻቸ። ያ ኃይልም ቀስ በቀስ እየተጠናከረና ሀብት እያከማቸ ሄደ። በለጸገ። በተለይ ነጋዴው። የንግድ ስርዓቱ በመዛባቱ ሁሉም ነጋዴ አይደለም የከበረው፣ ወይም የሚከብረው። ከገዢ ፓርቲው

ባለሥልጣናትና ከመንግስት ጋር የተቆራኘው ነው በልቶ እያበላ፣ ስኳር ልሶ እያላሰና መንግስታዊ መዋቅሩን እያነቀዘ በአቋራጭ የከነፈው።

ይህ ዘራፊ መንግስታዊ አካል፣ የጀመረው ስራ እንዲፋጠን አዳዲስ ፖሊሲዎች፣ አሰራራና መላዎች ነደፈ፡፡ ከ1997 ዓም ምርጫና አፈና በኋላ የነበረው ጊዜ፣ ምቹ ሁኔታን ስለፈጠረለት የፖለቲካ ምህዳሩን አጠበበ። 1 ለ 5 የተሰኘ የአፈና አሰራር ዘረጋ። ሃሳባቸውን በነፃነት የሚገለጹ ሙያተኞችና ዜጎች ታፈኑ። ሙስናን ለመቋቋም ሊረዱ የሚችሉ የሚድያ አካላት አንድ በአንድ እየተዘጉ ሄዱ፣ ወዘተ። ሙስናም መረን ለቀቀ።

በመንግስቱ ውስጥ ያሉ ችግሮችን በተመለከተ ጥናት እንዲያጠና በራሱ በመንግስቱ የተመደበ ቡድን፣ ኢህአዴግ መራሹ መንግስት ምን ያህል በሙስና ውስጥ እንደተዘፈቀ ዘገበ። ይህ በኢህአዴግ ላይ የቀረበው ሃሳብ ወራሹ ብልጽግናን ይመለከታል፤ እንዲህ ይላል

- "…የህገ ወጥ ደላሎች (ቁጥር) ከፍተኛ ነው። ባየናቸው ክልሎች ሁሉ የደላሎች መብዛት በጣም ወሳኝ ሆኖ ነው ያገኘነው። ደላላ ይፈርዳል የሚባልበት ሁኔታም አለ። እኛም ሄደን ስናነጋግር የመሬት ጉዳይ ከሆነ ሄዳችሁ ደላላ ብታነጋግሩ ይሻላችኋል ብለውናል፤"
- "…መሬትን በተመለከተ በአቋራጭ የሚከብሩበት መንገድ ጭምር እየተፈለገ ነው። የመምሪያዎችን ቀዳዳ በመፈለግ።
- "…ቡድነኝነት አብዛኛው ቦታ ይንጸባረቃል። የአንድ አካባቢ ሰዎችን ብቻ ተጠቃሚ ለማድረግ ይሞከራል።"
- "…ጉቦ ለማግኘት በማሰብ ሆን ብሎ ግለሰቦችን ማሰር።"
- "…ከፍተኛ አመራር ጣልቃ መግባት፤ 'ይሄን ፋይል ዝጋ፣ ምርመራ ከተጀመረም አቁም' ይባላል።
- "…እስረኞችን ከታሰሩበት ቦታ አንስተው ሌላ ቦታ ይወስዷቸዋል። በዚህ ጊዜ፣ እንዲመልሷቸው በገንዘብ ድርድር ይመጣል።"
- (በኢፌድሪ የጥናትና ምርምር ማዕከልና በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ሚኒስቴር የጋራ ትብብር የተደረገ ጥናት - አቶ ተካ ገ/እየሱስ - በዋልታ ተዘጋጅቶ ዩቱዩብ በቪድዮ ተቀርጾ የተገኘ የ48 ደቂቃ ቅጅ)

ከላይ የተጠቀሰው ዘገባ የሙስናውን ስፋት ነው የሚያሳየን።

## የአዲሱ የገዢ ቡድን ልዩ ባህሪዎች

የ1966 ዓም ንቅናቄ መቋጨያ የሆነውና በሕወሃት/ኢህአዴግ ጉያ ስር በመፈጠር ላይ ያለው ገዢ ቡድን ከተወሰነ ስልተ ምርት (mode of production) ጋር ተያይዞ የሚያድግና ራሱን ችሎ የሚቆም ሳይሆን፣

በመንግስት ስር ባሉ የኢኮኖሚ ተቋማት፣ በፖለቲካ ድርጅቶቹ፣ በወታደራዊ ኃይሉ፣ በቤተሰብ፣ በነጋዴዎች፣ ወዘተ ዙሪያ የተፈጠረና እየተጠናከረ በመሄድ ላይ ያለ አካል ነው። ከስልተ ምርት ጋር የተያያዘ ህልውና የሌለው ተለጣፊ ፍጡር ነው።

የዚህ አካል አባላት በራሱ በመንግስቱ ከፍተኛ እርከን ውስጥ የሚገኙ ግለሰቦችንም የሚያካትት ሲሆን፣ በተለምዶ መንግስታዊ ከበርቴ ተብሎ ይጠራል። ይህ ቡድን ቁልፍ የሆኑ የመንግስት እና በድርጅቶቹ ዙሪያ ያሉ የንግድ ተቋማትንና የሥልጣን ቦታዎችን ስለሚቆጣጠር ጥቅሙን ለማስጠበቅ አስፈላጊ ህጋዊ ከለላዎችንና ሁኔታዎችን ያዘጋጃል። ያመቻቻል። ለተባባሪዎቹ መረጃዎች ያቀብላል፣ ይጠቁማል። በመንግስቱና በድርጅቶቹ ዙሪያ የተፈጠረው ይህ አካል፣ ብቻውን መስራት አይችልምና ከመንግስቱ ውጭ ሆኖ የሚተባበረው አካል ይፈጥራል፣ ተፈጥሯልም። ጥናት ያቀረቡት ምሁራን ደላላዎች በማለት የጠቀሱት ያንን ክፍል ሲሆን፣ በዘመናዊ መጠሪያው ያ አካል አቀባባይ ከበርቴ ተብሎ ይፈረጃል። ደላላም ተባለ አቀባባይ ከበርቴ፣ ዋና ስራው የመንግስታዊ ከበርቴው ሥልጣኑን መከታ በማድረግ ከመንግስትም ሆነ ከሌሎች አካላት ሊገኙ የሚችሉ ውሎችን፣ መሬትን፣ ሸቀጦችን፣ ጥቅማ ጥቅሞችን፣ ወዘተ፣ አሰናድቶና አመቻችቶ፣ በተጨማሪ፣ ለህጋዊ ተግዳሮቶችም ይሁን ለሌላ ህጋዊ ጥያቄዎች ምላሽ አዘጋጅቶ ሲጠብቅ፣ አቀባባይ ከበርቴው ገበያውን ያመቻቻል። ተቀባይ ያዘጋጃል። ሸቀጦቹንም ሆነ ዕቃዎቹን የሚገዛው መንግስት ከሆነም፣ ዕቃ የሚያቀርብ ያመጣል። ይህ የአቀባባይ ከበርቴ (ደላላ) ቡድን፣ በመንግስታዊ ከበርቴውና በተቀባዩ ወይም በአቅራቢው መሀል በመሆን የንግድ እንቅስቃሴውን በቅርብ ይከታተላል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል። እነዚህ ሁለት የከበርቴ ቡድኖች አንዱ ያለሌላው አይኖሩም። አይከብሩም። <u>በአሁኑ የኢትዮጵያ ሁኔታ፣ ጠቅላይ ሚንስቴር ዶ/ር ዐብይ አህመድ እንደሚሉት የችግሮቹ ምንጭ ግለሰብ 'ሌቦች' ሳይሆኑ፣ በፓርቲዎቻቸው ውስጥና ዙሪያ፣ እንዲሁም በመንግስታቸው ውስጥ ከከፍተኛ እስከ ዝቅተኛ እርከኖች ውስጥ የበቀሉና የሚገኙ ግለሰቦችና በንግድ ሥርዓቱ ውስጥ ያለው የከበርቴ ቡድን ነው።</u> በጉዳዩ ላይ የችግሩን ብልት ሊደርሱበት ካልቻሉና መፍትሄ ካላበጁ፣ በሌሎች አገሮች እንደተደረገው ሁሉ ወይ ተባባሪው ያደርጋቸዋል፣ ካልሆነም ይቀረጥፋቸዋል፡፡ እዚህ ላይ ግብጽን ልብ ይሏል፡፡ የ1950ዎቹ የግብጽ ንቅናቄ መሪ ገማል አብድል ናስር እንዳረፉ የተተኩት ሳዳት፣ ሙሉ በሙሉ የገዢው መደብ ታዛዥ ሊሆኑ እንደቻሉ በርካታ የምርምር ስራዎች መዝግበዋል፡፡

የኢትዮጵያ የንግድም ሆነ የኢኮኖሚ፣ እንዲሁም የፖለቲካ ችግሮች ከዚህ የከበርቴ ቡድን አሰራር ጋር የተያያዙ ናቸው። አዲስ የተፈጠረው ቡድን በፊት የሕወሃት/ኢህአዴግ አሁን ደግሞ የኦህዴድ/ብልጽግና ፍጥሩ እንደመሆኑ

መጠን፣ እንደ አልቅት ከድርጅቶቹ ጋር ተጣብቷል። ይህ ቡድን በመንግስት ላይ ጥገኛ እንደመሆኑ መጠን ብዛቱንና ጉልበቱን መናገር ባይቻልም፣ ሰፋ ያለ የጥቅም ተጋሪዎች እንዳሰባሰበ መገመት ይቻላል። ከላይ የተጠቀሰው ጥናት ከጥቂት አመታት በፊት በቀረበበት ስብሰባ ላይ ጠቅላይ ሚንስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ባደረጉት ንግግር እንደገለጹት፣ ምናልባት ከጥቂት ሰዎች በስተቀር፣ ብዙ ባለሥልጣናት በአንድ ወይም በሌላ መልክ ይህ የከበርቴ ቡድን ከሚያካሂደው መጠነ-ሰፊ ሙስና ጋር ስለተሳሰሩ፣ ሥርዓቱ ላይ ያነጣጠረ የመፍትሄ ዘዴ ችግሩን ማጥፋት ቀርቶ መቅረፍ እንደማይችል ጥርጣሬአቸውን ግልጸዋል። ይህ እሳቸው የገለጹት ሃሳብ ዛሬ ሊቀየር አይችልም፡፡ የትናንትናው ኢህአዴግና የዛሬው ብልጽግና፣ መለስተኛ ለውጦችና አንዳንድ መኳኳሎች ከመደረጉ በስተቀር መሰረታቸው አንድ ነው፡፡

ትናንትም ሆነ ዛሬ፣ አዲሱ ቡድን፣ በወታደሩም ሆነ በሲቪሉ የመንግስት አካላት ውስጥ ፍላጎቱንና ጥቅሙን የሚያስጠብቁለት እንጅ የሚቃወሙትንና ሊያደናቅፉት የሚሹ ባለሥልጣናትን በሃላፊነት ቦታ ላይ እንዳይቆዩ የሚችለውን ሁሉ ያደርጋል። ከሆነለት አፋቸውን እንዲዘጉ፣ ያ ካልሆነም ከቦታቸው እንዲነሱ ይጥራል። እነዚህ መለስተኛ መፍትሄዎች የማይሰሩ ከሆነም፣ በወታደሩና በስለላ ድርጅቱ ውስጥ ባሉ ተባባሪዎቹ አማካይነት ጉልበት እስከመጠቀም የደረሰ እርምጃ ሊወስድ ይችላል።

ቀደም ሲል እንደተጀመረው ሁሉ፣ አዲሱ ቡድን፣ የኢህአዴግ/ብልጽግናን ፖሊሲ መከታ በማድረግ ደሀውን ከቦታው እየነቀለ ከመካከለኛ ምስራቅ፣ ከሕንድ፣ ከቻይና፣ ወዘተ ለሚመጡ ባለሀብቶች እጅግ ርካሽ በሆነ ዋጋ መሬት መቸብቸቡን ይቀጥላል፡፡ ከመሬቱ የሚገኘው ምርትም የኢትዮጵያ ገበያዎችን ሳይሆን ሰማዩን አቋርጦ ወደ ባህር ማዶ ይሻገራል። ይህ በብዙ የአፍሪቃ አገሮች በመስፋፋት ላይ ያለው የመሬት ቅርሚያ በድንገት የመጣ ሳይሆን፣ "በ19ኛው ክፍለ ዘመን እንደተካሄደው የቅኝ አገዛዝ ፖሊሲ ተመስርቶ የተነደፈ ነው።" (Land Grab in Africa: *Emerging land system drivers in a teleconnected world*፣ Cecilie Friis & Anette Reenberg፣ GLP Report No. 1፣ pg. 8)

ለአዲሱ የመሬት ቅርሚያ አንዱ ምክንያት፣ ለምግብ ፍጆታቸው በውጭ ንግድ ላይ የሚተማመኑ አገሮች እአአ በ2007-2008 ዓም የደረሰባቸው የምግብ እጥረትና አቅርቦት ሲሆን፣ ያን ችግር ለማሻሻል ሲባል ፖሊሲው ተነደፈ። ከዚህ በተጨማሪ፣ ከጥቂት አመታት በኋላ በዓለም ዙሪያ በተለይም እንደ ቻይና በመሳሰሉ አገራት የሕዝብ ቁጥር በከፍተኛ ፍጥነት ያድጋል ተብሎ ይገመታል። እአአ በ2010 ዓም 6.8 ቢሊዮን የነበረው የዓለም የሕዝብ ቁጥር

እአአ በ2050 9.2 ይደርሳል ተብሎ ተገምቷል። እነ ሳውዲ አረቢያም የመሬት ጥበት ይገጥማቸዋል። (Land grab in Africa: Emerging land system drivers in a teleconnected world. GLP Report No. 1. Page 4)

G-8 በመባል የሚጠራው የበለጸጉ ሀገሮች ስብስብ ባወጣው፣ "New Alliance for Food Security and Nutrition in Africa" and the Alliance for a Green Revolution in Africa (AGRA) በተባለው እቅድና ፖሊሲዎች መሰረት፣ ለውጭ ባለሀብቶች የሚስማማ ህግ፣ የመሬት ባለቤትነት ሥርዓቱ ለባለሀብቶቹ የሚጠቅምና ዘረ-መላቸው የተቀየረ (GMO's) ዘሮች መትከል ይቻል ዘንድ ሁኔታዎች ተመቻችተዋል። በአሁኑ ጊዜ የአፍሪቃን መሬት በመቀራመት ላይ ያሉት የቀድሞዎቹን የቅኝ ገዢዎች ጨምሮ እንደ እነ ሳውዲ አረቢያ ያሉ የአረብ አገሮች፣ ቻይና እና ሕንድንም ያጠቃልላል። ለመሬት ነጠቃ የሚመቹ አገሮችን ለይቶ ለማውጣት፣ ዓለም ባንክ 14 አገሮችን የሚመለከት ጥናት አደረገ። በደረሰበት መደምደሚያ መሰረትም፣ ባለሀብቶቹ የሚመርጡት አገር፣ "…አስተዳደሩ ደካማ፣ ፖለቲከኞቹ ሙስና ውስጥ የተዘፈቁና ባለመሬት የሆነው ሕዝብ መብት ሲጣስ ህጉም ሆነ ሥርዓቱ በበቂ ሊከላከል የማይችሉ መሆናቸው" ነው። **(Policy Brief 041 | June 2011 www.future-agricultures.org Land Grabbing in Africa and the New Politics of Food)**

መሬት ሙሉ በሙሉ በማዕከላዊ መንግስት ስር በመሆኑ ህዝቡን እንደፈለገ ያፈናቅላል። ቀደም ባለው ጊዜ ይህ እርምጃ የሚወሰደው በዲቬሎፕመንታል ዴሞክራሲ ስም ሲሆን፣ በሕወሃት/ኢህአዴግ ዙሪያ እየተፈጠረ ያለው አዲሱ ቡድን መሬትን ለውጭ ባለሀብቶች በእጅ መንሻነትም ጭምር ይሰጣል።

## በብልጽግና ዘመንስ

የመሬት ማፈናቀሉ ቀጥሏል፡፡ በሺዎችና አስር ሺዎቹ የሚቆጠሩ ዜጎች ብዙ ዘመናት ከነበሩባቸው ቀያቸው እንዲሰደዱ ተደርገዋል፡፡ ዘር ጥላቸውና በዘር ላይ ያተኩሩ ጥቃቶች ከመቼውም ጊዜ በላይ ጨምሯል፡፡ በእድሜ ዘመናቸው ያፈሯቸው ንብረቶቻቸውን ተነጥቀው የድሃ ድሃ ሆነዋል፡፡ ይህ ሁኔታ በወለጋ ውስጥ በስፋት የተፈጸመ ሲሆን በሌሎች አካባቢዎችም ተካሂዷል፡፡

## ኢህአዴግና ብልጽግና አንድነትና ልዩነት

የብልጽግና ፓርቲ ከኢህአዴግ አብራክ የወጣ ከመሆኑም በላይ በሁለቱ መሀል ያለው ልዩነት፣ ሀ/ በኢህአዴግ ጊዜ አድራጊ ፈጣሪ የነበረው ህወሃት የብልጽግና አባል አለመሆን፣ ለ/ በኢህአዴግ ጊዜ ተለጣፊ ተብሎ ይቆጠር የነበረው የኦሮሞ

ብልጽግና ድርጅት በአሁኑ ወቅት ህወሃትን በመተካት አድራጊ ፈጣሪ መሆን፣ ሐ/ በኢህአዴግ ውስጥ አራት ድርጅቶች ብቻ የነበሩ ሲሆን፣ በብልጽግና ግን በተባባሪነት ይሳተፉ የነበሩት ሙሉ አባል በመደረጋቸው የድርጅቱ አባላት ቁጥር መጨመር፣ መ/ የኢህአዴግ መመሪያ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የነበረ ሲሆን፣ የብልጽግና ግን መደመር በሚል እሳቤ ላይ የተመሰረተ መሆንና የመሳሰሉት ናቸው ልዩነቶቹ፡፡ አንድነቶቹን ስንፈትሽ ደግሞ፣ ሀ/ በዋነኛነት፣ ኢህአዴግም ሆነ ብልጽግና ብሄር/ብሄረሰብን ወይም ማንነትን መሰረት አድርገው የተፈጠሩ ናቸው፡፡ የትናንትናው ኦህዴድ፣ ብአዴን፣ ወዘተ፣ መለስተኛ የስምና ሌላ ለውጥ አድርገው ስራቸውን ቀጥለዋል፡፡ ትናንት ኦሮሞዎችን ብቻ ያቀፈው ኦህዴድ፣ ዛሬም ያው ነው፡፡ የአማራው፣ የሱማሌው፣ ወዘተ፣ ድርጅቶችም ሁሉም በማንነት የተደራጁ ናቸው፡፡ ይህ የማንነት ጉዳይ መለያቸው ብቻ ሳይሆን፣ ቁልፍ የሆነው የርእዮታቸው፣ የአስተሳሰባቸው፣ የፖሊሲያቸው፣ ወዘተ፣ ምንጭ ነው፡፡ በዘር ላይ የተመሰረተ ድርጅት አባል የሆነ ማንም ኃይል ከራሱ ማንነት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች እንጅ በሌሎች ላይ አያተኩርም፡፡ ኢህአዴግንና ብልጽግናን አንድ የሚያደርጋቸውና የሚያመሳስላቸውም ይኸው ጉዳይ ነው፡፡ የብልጽግና ድርጅት የኢህአዴግ ሌላ ገጽታ ነው፣ ወይም ኢህአዴግ ቁጥር ሁለት ነው ቢባልም ሊያስገርም አይችልም፡፡ በኢህአዴግም ሆነ በብልጽግና ዘመን የየድርጅቶቹን የባላይነት የተቆጣጠረው ኃይል በማንነት ላይ የተመሰረተ ተረኛነት የሚያስተናግደውም የሁለቱም አካሎች መሰረት አንድ ስለሆነ ነው፡፡ ለ/ ከህወሃት መወገድ በስተቀር፣ 95 በመቶ በላይ ሊሆን የሚችለው የብልጽግና መዋቅር ከኢህአዴግ የተወረሰ ነው፡፡ ከጥቂት የሰዎች ሽግሽግና ለውጥ በመለስ፣ ከዝቅተኛ መዋቅሮች ጀምሮ እስከ ከፍተኞቹ ድረስ ያሉት አባላት ስብጥር ተመሳሳይ መሆኑን መገመት ይቻላል፣ ሐ/ ከህወሃትና በከፊል ከብአዴን በስተቀር አብዛኞቹ የየድርጅቶቹ አባላት የተመለመሉት ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ በኋላ ሲሆን፣ ይህ ሁኔታም በድርጅቱ አሰራርም ሆነ አካሄድ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ በትግል ዘመኑ አንድ ድርጅትን የሚቀላቀሉ አባላት፣ መርሃ ግብሩን አምነውና ተቀብለው፣ መስዋዕትነት፣ ህይወት የሚጠይቅም ጭምር፣ ለመክፈል ተዘጋጅተው ነው፡፡ ያ ድርጅት ስልጣን ከያዘ በኋላ የሚቀላቀሉ ግን፣ መርሃ ግብሩን የተቀበሉ ቢኖሩበትም በአመዛኙ ከመንግስት የሚገኘው ጥቅምን ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ ቀዳሚውና የመጀመሪያ ትኩረታቸው ራሳቸውን ማበልጸግ መሆኑ ሊያስገርም የማይችለውም ለዚህ ነው፡፡

## የማንነት ፖለቲካና አዲሱ ቡድን

አዲሱ ቡድን ዋና ዓላማው ሀብት መዝረፍና ማጋበስ ነው፡፡ የማንነት ፖለቲካ የሚጠቅመው ከሆነ እስከ መጨረሻው ሊያስጮኸው ይችላል፡፡ ይገለገልበታል፡

፡ ሲሻው ብሄረተኛ፣ ወይም የአንድነት ኃይል ሆኖ ብቅ ሊል ይችላል፡፡ ጽንፈኝነት የተጸናወተው ቡድን ሁለግዜም ጠላት ይፈልጋል፡፡ ፍቅር ሳይሆን ጥላቻ ይቀፈቅፋል፡፡ አንድነትንና የጋራነትን አያውቃቸውም፡፡ ልዩነትንና ጥላቻን ካልሰበከ ህልውናው ሊያከትም ይችላል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ጠላት ተደርጎ የሚሳለው ከማህበረሰቡ ውጭ የሆነ ወይም ከውጭ የመጣ ሊሆን ይችላል፡፡ በተለያየ ዘመን በዓለም ዙሪያ የተነሱ የብሄርተኝነት ፖለቲካ አራማጆች ዋነኛ መገለጫም ይኸው ነው፡፡ ሩዋንዳን፣ ዩጎዝላቪያን፣ ጀርመንን፣ ወዘተ፣ ይጠቅሷል፡፡

## ሐ/ የት ደርሰናል? ሀገራዊ ግንባታ

ሀገራዊ ግንባታ ሁለት ዘርፎች አሉት፣ ሀገረ-መንግስታዊ ግንባታና (state formation) እና ሀገራዊ ግንባታ (nation building) ናቸው:: ሀገረ መንግስታዊ ግንባታ ለመሰረተ ልማት ቁልፍ የሆኑ ግብዐቶችን መፍጠር፣ መቆርቆር፣ መዘርጋት፣ ወዘተ ላይ የተመሰረተ ሲሆን፣ እንደ መንገድ፣ ቴሌፎን፣ መብራት፣ ኢንተርኔት፣ ወዘተን ያጠቃልላል፡፡ ሀገራዊ ግንባታ ደግሞ ብሄራዊ ማንነትን መፍጠር ላይ የተመሰረተ ሲሆን፣ ታሪክ፣ ባህል፣ ጂኦግራፊና ሌሎች በርካታ ግብዐቶች ለግንባታው አስተዋጽኦ ያበረክታሉ፡፡ ከሞያሌ እስከ አሲምባ፣ ከኤለከሬ እስከ አሶሳ ያሉ ወገኖች የኢትዮጵያ ደስታ ደስታቸው፣ ሀዘኗ ሀዘናቸው የሚሆነው በቃላት ሊገለጽ በማይችል ሀገራዊ ስሜት ስለተሳሰሩ ነው፡፡ ሯጮቿችን አሸንፈው የኢትዮጵያ ባንዲራ በዓለም ፊት ሲሰቀል ይሄ ነው የማይባል ደስታ ሰውነታችንን የሚወረው የሀገራዊ ግንባታ ውጤት የሆነው የደስታ መንፈሳችን ሲነካ ነው፡፡ ለአንድ ኢትዮጵያዊ ሀገራዊ ግንባታ የአክሱም፣ የላሊበላ፣ የጎንደር ስልጣኔ፣ የገዳ ሥርዓት፣ ወዘተ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የነበራቸው ሲሆን፣ እርስ በእርስ ይካሄድ በነበረው ጦርነትም፣ አንዱ የበላይ ሲሆን ባህሉንና ቋንቋውን በሌላው ላይ በመጫኑ ሊከተል የሚችለው የመዋሃድና የመቀየጥ ሂደት፣ ወዘተ ለሀገራዊ ግንባታ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮም፣ ከዲሞክራሲና ከሕዝባዊ ሥርዓት ጋር ተሳስሮ ለሀገራዊ ግንባታ የተሻለ ዕድል ተፈጠረ፡፡

በታሪካዊ አጋጣሚነት ብቅ የሚሉ ክስተቶችም ለብሄራዊ ማንነትና ለሀገራዊ ግንባታ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ፡፡ በዘመነ መሳፍንት እጅግ ከፍተኛ የመፈረካከስ አደጋ ገጥሟት የነበረችው ኢትዮጵያ፣ በ19ክፍለ ዘመን ላይ ጣሊያን ሲወራት በጨለማ ውስጥ ቦግ ብሎ እንደሚታይ ብርሃን ኢትዮጵያን

አንድ ዕድል ገጠማት፡፡ በአድዋ ጦርነት ኢትዮጵያ ማሸነፏ ተራራዎቿንና ሸለቆዎቿን አቋርጦ በመላው ዓለም ናኘ፡፡ ኢትዮጵያውያን በሃሴት ተሞሉ፡፡ አድዋ ከታሪክ ማስታወሻነት ገዝፎ የሀገራዊ ግንባታ አካል በመሆን የማንነት መገለጫም ሆነ፡፡ አድዋ ማለት ኢትዮጵያዊነት ሆነ፡፡ የአድዋ አባት ምንሊክም ለዝንተ ዓለም በኢትዮጵያውያን አእምሮ ተቀርጸው እንዲኖሩ ታሪክ ፈቀደ፡፡ አድዋ በኢትዮጵያውያን ዐዕምሮ ታትሞ ቀረ፡፡ አድዋን መጎንተል ኢትዮጵያን ማጉደፍ ተደርጎ ይወሰድ ጀመር፡፡

ትናንት ላልነበሩ ህፃናት ጭምር አድዋ የእነሱም መገለጫ ሆነ፡፡ በ2013 ዓም የአድዋ በዓልን ለማክበር ወደ መስቀል አደባባይ ስሄድ በፈቃድ እንደሚገባ ተገለጸልኝ፡፡ ሁኔታው በጣም ስላስገረመኝ በአካባቢው ሆኜ መጨ ወራጁን ስመለከት፣ አንድ አምስት የሚሆኑ፣ በሃበሻ ቀሚስ ያሸበረቁ የ13 እና የ14 አመት ህፃናት አጠገቤ መጥተው፣ "ፋዘር፣ አድዋ የሚከበርበት ቦታ የት ነው" አሉኝ፡፡ መግቢያውን አመላከትኳቸውና "ግን አያስገቧችሁም" አልኳቸው፡፡ "እኛ እሱን አንፈልግም፣ ዋናውን ነው የምንፈልገው" አሉኝ፡፡ "እሱማ ሩቅ ነውኮ፣ ጊዮርጊስ ነው" አልኳቸው፡፡ ትራንስፖርት አልነበረምና ከመስቀል አደባባይ እንዴት አደርገው ጊዮርጊስ ሊደርሱ እንደሚችሉ በማሰብ ነበር ሩቅ ነው ያልኳቸው፡፡ "ፋዘር ለአድዋ የሚከፈለውን እንከፍላለን" ብለውኝ እየሳቁና እየፈነጠዙ ሄዱ፡፡ ሁኔታቸው ገርሞኝ ከአይኔ እስኪጠፉ ተከተልኳቸው፡፡

በተጨማሪ፣ ለሀገራዊ ግንባታ ቋንቋ ትልቅ ቦታ አለው፡፡ ለማሳያነት፣ በ19ኛው ክፍለ ዘመን፣ ከፈረንሳይ ልጆች መሀል ግማሹ እንኳን ቋንቋውን መናገር አይችሉም ነበር፡፡ ፈረንሳይ ብዙ ቋንቋዎች የሚናገሩባት ሀገር የነበረች ስትሆን፣ የፈረንሳይ መንግስትም የተጠላ ነበር፡፡ ሁኔታው የተቀያየረው ከፈረንሳይ አብዮት በኋላ መሪዎቹ የፈረንሳይ ማንነትን ለመገንባት ሰፊ ስራ ካካሄዱ በኋላ ነበር፡፡ የፈረንሳይኛ ቋንቋን በስፋት አስተማሩ፣ እናም ዛሬ ቋንቋው ፈረንሳይ ውስጥ ብቻ ሳይሆን፣ ቅኝ ግዛቶቻቸውም ፈረንሳይኛ ተናገሪ ሆነዋል፡፡

የታንዛንያው ኔሬሬ ሁለት አገሮችን ቀላቅለው፣ (ታንጋኒካንና ዛንዚባርን) በሀገሪቱ ውስጥ የማንነትም ሆነ ማናቸውም ዓይነት ጥላቻና መፈራቀቅ እንዳይኖር፣ ለማንኛውም የህዝብ ክፍል የተለየ እንክብካቤ እንዳይደረግ በማሰብ ኡጃማ በተባለው ፖሊሲያቸው ተመስርተው ባካሄዱት ሰፊ ዘመቻ የታንዛንያን ሀገራዊ ማንነት ገነቡ፡፡ ለኔሬሬ ፖሊሲ ስኬት፣ የገዢ ፓርቲው የታንጋኒካ አፍሪካን ናሽናል ዩኒየን ዋነኛ መርህ፣ "በአፍሪቃውያኖች መሀል አንድነትና

ህብረት እንዳይኖር እንቅፋት ሊሆን የሚችለውን ጎሰኝነትንና ማናቸውንም ዓይነት ለአንድነት የሚደረግ እርምጃ ላይ የሚታይ ጥላቻን መታገል ነው" አለ፡ ፡ (Miguel 2004, Abdulaziz 1980).

ሀገራዊ ግንባታንም ሆነ አንድነትን ለማምጣት ሁሉም ሀገሮች በአብዛኛው ጦርነትን መገልገያ አድርገዋል፡፡ የጀርመኑ ቢስማርክ፣ የአሜሪካው ሊንከን፣ የቱርኩ ከማል አታቱርክ፣ የኢጣልያው ጋሪባልዲ፣ ወዘተ በዚህ ሂደት አልፈዋል፡ ፡

የኢትዮጵያው አጼ ምንሊክም አንዱ ናቸው፡፡ የታሪክ ግጥምጥሞሽ ሆኖ ከደርቡሽ ጋር ሲዋጉ ባይወድቁ፣ አጼ ምንሊክ ያደረጉትን አጼ ዮሐንስ ሊያደርጉት ይችሉ ነበር፡፡ ወይም፣ የወላይታው ጦና፣ የጅማው አባ ጅፋር፣ የከፋው ንጉስ ጨኒቶ፣ የወለጋው ጆቴ ሊሆኑ ይችሉ ነበር፡፡ ያ በዚያን ጊዜ የተፈጸመው በአሁኑ ዘመን ካላነው ቁጥጥር ውጭ በመሆኑ፣ ታሪክን ለመቀልበስ መሞከር ሳይሆን፣ የተበላሸውን እንዴት እናቃና ብለን ማሰብ ነው ያለብን፡፡ የአሜሪካ ጥቁሮች፣ የመምረጥ መመረጥ መብታቸውን ለማስከበር፣ ከመቶ ሃምሳ አመት በላይ ትግል ጠይቋቸዋል፡፡ እናም፣ ሀገራዊ ግንባታ ሆደ ሰፊነትንና ትዕግስትን የሚጠይቅ የረዥም ጊዜ ሂደት ነው፡፡

በተጨማሪ፣ ሀገራዊ ግንባታ የምርጫ ጥያቄ አይደለም፡፡ እንደ ሀገረ-መንግስታዊ ግንባታ ታስቦና ታቅዶ የሚሰራ ሳይሆን፣ መንግስት በሚከተላቸው ቀና ፖሊሲዎች ላይ፣ በተለይም በዲሞክራሲና በሕዝባዊ ሥርዓት ላይ ተመስርቶ የሚገነባ፣ እንደ አድዋ ልዩ ታሪካዊ አጋጣሚዎች ታክለውበት የሚጎለብት ነው፡ ፡

ህወሃት ኢትዮጵያን ለማጥፋት ያካሄደው መጠነ-ሰፊ ውጊያ ያልጠበቀውና ያላሰበው ሁኔታ እንዲፈጠር ግድ ብሏል፡፡ የኢትዮጵያ ባንዲራ ከፍ ብሎ ሊውለበለብ ቻለ፡፡ ከጽንፈኛ ብሄረተኞች በመለስ ሁሉም የኢትዮጵያ ዜጎች በቁጭትና በብስጨት ገበኑ፡፡ አቅሙ የነበራቸው በጦር ሜዳ ተሰለፉ፣ በወታደርነት ተመለመሉ፡፡ ስንቅ አዘጋጁ፡፡ ልጆቻቸውን መርቀው ሸኙ፡፡ በጦርነቱ የወደቁ የአማራ፣ አፋር፣ ወላይታ፣ ወዘተ፣ ልጆች እንደተቃቀፉ በአንድ ጉድጓድ ተቀበሩ፡፡ የህወሃት ትንኮሳ ኢትዮጵያዊነትን አጎለበተ፡፡

## ጽንፈኛ ብሄረተኝነትና የሀገር ግንባታ

ለሀገራዊ ግንባታ እንቅፋት ከሚሆኑ ሳንካዎች መሀል አንዱ ልዩነትን የሚቆፈቅፈው ጽንፈኛ ብሄረተኛነት ሲሆን፣ ይህን የሀገር አደጋ ሳይታክቱ መታገልና ስረ መሰረቱን መንቀል ከዘመናችን ትልቁ ስራዎች መሀል አንዱ ነው፡፡ ጽንፈኛ ብሄረተኝነት ካልተዳከመ የልዩነትና የጥላቻ መርዝ በመልቀቅ ህዝቦች እንዳይቀራረቡ ያደርጋል፡፡፡

ከዚህ በተጨማሪ፣ በግፍ፣ በዘረኝነት፣ በስግብግበነት ላይ የተመሰረተው የመሬት መቀራመት፣ ኢትዮጵያን በማድማት ሀገራዊ ግንባታው ላይ ከፍተኛ አደጋ ጋርጧል፡፡

## መ/ የት ደርሰናል? የእኩልነት ጥያቄ

የያ ትውልድ ቀደምት አባላት ገና ህፃናት በነበሩበት ጊዜ የተቀሰቀሰው የእኩልነት ጥያቄ ሁነኛ መፍትሄ ሊበጅለት ባለመቻሉ እስከ ዛሬ ድረስ ዘልቋል፡ ፡ በ1940ዎቹና 50ዎቹ አመታት ከተቀሰቀሱት ቀደምት እንቅስቃሴዎች መሀል የቀዳማዊ ወያኔ፣ የባሌ አርሶ አደሮች የትጥቅ አመጽ፣ ኤርትራውያን መጀመሪያ ፌደሬሽናቸውን ለማስመለስ በኋላ ደግሞ ለነፃነት ያደረጉት እንቅስቃሴ፣ የሜጫና ቱለማ ማህበር መመስረትና የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡ እነዚህ ቀደምት የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ዕልባት ሊበጅላቸው ስላልቻለ እየተንከባለሉ ሲሄዱ ቆይተው የያ ትውልድ ዘንድ ደረሱ፡፡

በ1960ዎቹ አጋማሽ ላይ ሌሎች ብሄረተኛ ኃይሎች የኢትዮጵያን የፖለቲካ ትግል ተቀላቀሉ፡፡ የኦሮሞ፣ የትግራይና የሲዳማ ነፃ አውጭ ግንባሮች ተቋቋሙ፡ ፡ "ብሄር/ብሄረሰባችን" በሃይማኖት፣ በቋንቋ፣ በባህል ወዘተ፣ ስለተጨቆነ፣ ከመሬት ጋር ተያይዞም ከፍተኛ በደል ደርሶበት እሮሮውን ሊያዳምጥለት የሚችል አካል ባለመኖሩ በራሳችን ትግል ሕዝባችንን አርነት እናወጣለን በሚል እሳቤ ተነሳሱ፡፡ ሁሉም በሚባል ደረጃ ከተማሪ እንቅስቃሴው አብራክ በወጡ ወጣቶች አማካይነት ሲሆን ሊቋቋሙ የቻሉት፣ ከሲዳማው በስተቀር የተቀሩት የትጥቅ ትግል ለመጀመር ዝግጅቶች ማድረግ ጀመሩ፡፡

እነዚህ ብሄረተኛ ኃይሎች በተነሱበት ወቅት፣ የያትውልድ አባላትም፣ ከ1960ዎቹ የመጀመሪያ አመታት ጀምሮ መፍትሄ መሻት ጀመሩ፡፡ ድርጅት ሲያቋቁሙም፣ የእኩልነት ጥያቄ መፍትሄ ከሚያሻቸው ጉዳዮች አንዱ በመሆኑ በመርሃ ግብራቸው ውስጥ ሰፈረ፡፡

ብሄረተኞቹም ሆኑ ህብረብሄራዊ ድርጅቶቹ፣ ሁሉም በየፊናቸው ላመኑባቸው ጉዳዮች አቅማቸው በፈቀደ መጠን መታገል ጀመሩ፡፡ ፌዴሬሽናችን ይመለስ በሚል የተጀመረው የኤርትራ ብሄረተኞች ትግል፣ ውሎ አድሮ ለችግራቸው ሁሉ ዋነኛዋ ጠንቅ ኢትዮጵያ ስለሆነች ነፃ ኤርትራን መመስረት አለብን በማለት በትጥቃዊ ትግል ተሰማሩ፡፡ ሌሎች ብሄረተኛ ኃይሎች ደግሞ፣ "ሕዝባቸውን" ለከፋ ኑሮ የዳረገው አማራው ነው በማለት ምንዝሩን ከጌታው ያልለየ የፖለቲካ መስመር ነድፈው አቅማቸው የፈቀደውን አደረጉ፡፡ በአማራው ላይ ሰፊ ቅስቀሳ ተደረገ፡፡ ከዚህ ወቅት ጀምሮም አማራው እንደ ሕዝብ በጠላትነት ተፈረጀ፡፡

በአንፃሩ፣ ኢትዮጵያ ዘርፈ-ብዙ ችግሮች የነበሩባት መሆኑን የተረዱት የያ ትውልድ አባላት፣ ህልውናዋን ለማስጠበቅም ሆነ በሀገሪቱ ሰላም ለማውረድ፣ እንደሌሎቹ ዐበይት ጥያቄዎች ሁሉ ለእኩልነት ጥያቄም መፍትሄ ማበጀት ሊታለፍ የማይችል ጉዳይ ነው በማለት መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴ አደረጉ፡፡ ጥያቄው ከሥርዓቱ ጋር የተያያዘ እንጅ የአንድ ህብረተሰብ ጉዳይ አይደለም ብለው የሚያምኑት የያ ትውልድ አባላት ችግሩን ከስረ መሰረቱ ለማስወገድ የሥርዓት ለውጥ ላይ ያተኮረ ትግል አደረጉ፡፡ ብሄረተኛ ኃይሎቹ አማራን በጠላትነት ፈርጀው ሲንቀሳቀሱ፣ የያትውልድ አባላት ደግሞ ዋነኛ ጠላት የውጭ ጣልቃ ገቦችና፣ ማለትም ኢምፔሪያሊዝምና ፊውዳሊዝም ናቸው አሉ፡፡ ብሄረተኛ ኃይሎቹ በአማራ ላይ ዘመቻቸውን ሲቀጥሉ፣ የያ ትውልድ አባላት የሥርዓት ለውጥ ላይ አተኮሩ፡፡

የሥርዓት ለውጥ እንዲመጣ ሲታገሉ በነበሩት የያ ትውልድ አባላት ላይ ደርግ ልዩ ትኩረት አድርጎ የፍጅት ሰለባ አደረጋቸው፡፡ የያ ትውልድ ትግል መዳከምም መድረኩ ለብሄረተኛ ኃይሎችና ለደርግ ሊለቀቅ በመቻሉ፣ ሁለቱ ሲፋለሙ ቆዩ፡፡ በዚህ መሀል ኢትዮጵያ የቀዝቃዛው ጦርነት አንድ አካል ሆና፣ የምዕራቡ ዓለም የበላይነቱን ሲጎናጸፍ፣ በዓለም ዙሪያ ይደግፏቸው የነበሩ እንደ ወያኔ ሃርነት ትግራይን የመሳሰሉ ብሄረተኛም ሆኑ ሌላ የፖለቲካ መስመር ይከተሉ የነበሩ ኃይሎች ድል ተጎናጸፉ፡፡ ኢትዮጵያም በብሄረተኛ ኃይሎች እጅ ወደቀች፡፡ ዕጣ ፈንታዋ የሚወሰነው በእነሱ ሆነ፡፡ ከዚያም፣ በመላ ኢትዮጵያ የብሄረተኞች የፖለቲካ ድርጅቶች ተቋቋሙ፡፡ በህወሃት አምሳል ዘርን መሰረት አድርገው የተደራጁ ኃይሎች  የፖለቲካ ሥልጣን እንዲጨብጡ

ተደረገ፡፡ ህወሃት በሁሉም ክልሎች ተለጣፊ ድርጅቶችን በማቋቋም የበላይነቱን አረጋገጠ፡፡

ቀጣይ እርምጃም ይህን በመሬት ላይ የሚገኘውን ዕውነታ ለማረጋገጥ ህገ መንግስት ተነድፎ ፀደቀ፣ ስራ ላይም ዋለ፡፡

ማንነት ላይ ተመስርቶ ታህሳስ 1986 ዓም የፀደቀው ሕገ መንግስት፣ ሀገሪቱን በ9 ክልሎች ሸነሸነ። አከፋፈሉ፣ በሕዝቡ አሰፋፈር፣ ማንነት፣ ቋንቋና የሕዝቡ ፈቃድ ላይ የተመሰረተ ነው ቢባልም፣ (ሕገ መንግስት፣ 1986፣ አ 46 እና 47)፣ በአፄ ኃይለ ሥላሴም ሆነ በደርግ ዘመን በተለያዩ ክፍለ ሀገሮች (በአርሲ፣ ባሌ፣ ከፊል ሸዋ፣ ከፊል ወሎ፣ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ከፋ፣ ወዘተ) ውስጥ የሚገኙ የኦሮሞ ተወላጆች ቋንቋን መሰረት በማድረግ የኦሮምያ ክልል ስር እንዲጠቃለሉ ተደረገ። ኢህአዴግ ሥልጣን እስከያዘበት ወቅት ድረስ፣ ጎጃም፣ ጎንደር፣ ከፊል ወሎና ከፊል ሸዋ ይባሉ የነበሩ ጠቅላይ ግዛቶች ታጥፈው፣ የአማራ ክልል ተብለው ተሰየሙ። ሌሎቹም በተመሳሳይ መንገድ ተሸነሸኑ፡፡

ከላይ የተጠቀሰው የማካለል ውሳኔ ስራ ላይ መዋል እስከጀመረበት ጊዜ ድረስ፣ የትውልድ ሀረጋቸው ምንም ይሁን ምን፣ ጎንደሬ፣ ወሎዬ፣ የሐረር ሰው፣ ወዘተ የሚል፣ ከባቢን መሰረት ያደረገ ስሜት ዳብሮ ቆይቷል። ሕወሃት/ኢህአዴግ በነደፈው ህገ መንግስት መሰረት መደራጀት ሲጀመር፣ ያ ሂደት ተገትቶ ሕዝቦች ከብዙ አመት በፊት ወደነበሩበት ማንነታቸው እንዲመለሱ አደረገ። አማራውን፣ ትግሬውን፣ ኦሮሞውን ያስተሳስር የነበረው ወሎዬነት በህግ ተሰረዘ። ግን ሊጠፋ አልቻለም፡፡ አማራውን፣ ትግሬውን፣ ጉራጌውን፣ ሱማሌውን፣ ሃረሪውን ያስተሳስር የነበረው የሐረር ተወላጅነት ቀርቶ ክልሉ በአንድ ብሄረሰብ አስተዳደርና ስም ሲጠራ፣ ከዚያ የህብረተሰብ ክፍል ውጭ የመጡ ወገኖች ምን ሊሰማቸው እንደሚችል መገመት ከባድ አይሆንም።

በተጨማሪ፣ በአብሮነት ይኖሩ የነበሩ ብሄረሰቦች፣ መለያየትን መረጡ፡፡ ለምሳሌ ስልጤና ጉራጌ፣ ቅማንትና አማራ፣ ወዘተ፡፡ ለዚህ መነሾ የሚሆነው ህገ መንግስቱ ሲሆን፣ እንዲህ ይላል፣ "...ክልሎች ውስጥ የተካተቱት ብሔሮች፣ በሔረሰቦች፣ ሕዝቦች በማንኛውም ጊዜ የየራሳቸውን ክልል የማቋቋም መብት አላቸው"። (ኢትዮጵያ ህገ መንግስት፣ አ 47/2) አንድ የህብረተሰብ ክፍል፣ ብሄረሰብ ተብሎ ከተፈረጀ ጠርቀም ያለ የራሱ የዞን በጀት እንዲኖረው ይደረጋል። የየአካባቢው ልሂቃንም፣ ኮብራ መኪና፣ ቤት ወዘተ፣ ስለሚሰጣቸው ሂደቱን አጥብቀው ደገፉ፡፡ በመተሳሰር ላይ የነበረው ህብረተሰብ እንዲለያይና በዓይነ ቁራኛ እንዲተያይ አደረጉ፡፡

## ፌዴራሊዝምና የብሄር ብሄረሰቦች መብት

የፌዴራሊዝም ዋነኛ መሰረት በማዕከላዊና በክልል መንግስታት መሀል ያለው የስልጣንና የሃላፊነት ክፍፍል ሲሆን፣ የክልል መንግስታቱ በከባቢያቸው ደረጃ የፖለቲካ ነፃነት የተጎናጸፉና በህብቱ ላይም የመወሰን ስልጣን ሊኖራቸው ይገባል። የአካባቢው መንግስት የከባቢው የበላይ በመሆን የክልል ሕገ መንግስት አውጥቶ ያስተዳድራል፣ የክልል ምርጫ ያስተናግዳል፣ በልማት፣ በክልል ጸኘነት፣ በአካባቢ ጥበቃ፣ በትምህርት፣ በጤና ጥበቃና በመሳሰሉ ዘርፎች ይሳተፋል። በሌላ በኩል፣ የፌዴራል መንግስቱ ወታደሩን፣ ፀጥታውን፣ የውጭ ግንኙነትን፣ ሀገራዊ ኢኮኖሚውን፣ ወዘተ በበላይነት ይመራል።

የክልል መንግስት ለፌዴራሉ ግብር ያስገባል። ፌዴራል መንግስት በፊናው መንገድ፣ መብራት፣ ቴሌኮሙኒኬሽንና የመሳሰሉ የመሰረተ ልማት አውታሮች ለመዘርጋት ኃላፊነት ይወስዳል።

የኢትዮጵያን ሁኔታ በተመለከተ፣ ቋንቋዎች እኩል መሆናቸው ተደንግጓል፣ (ህገ መንግስት፣ አ 5/1)፣ አማርኛ የስራ ቋንቋ መሆኑ ተገልጿል። (አ 5/2 ) የዜጎችና የሕዝቦች ሰብዓዊና ዲሞክራሲያ መብቶች ይከበራሉ ተብሏል። (አ 10/2)

“ማንኛውም ሰው በግል የሚጽፋቸውና የሚጻጻፋቸው በፖስታ ቤት የሚልካቸው ደብዳቤዎች፣ እንዲሁም በቴሌኮሙኒኬሽንና በኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎች የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች አይደፈሩም” ህገ መንግስት (አ 26/2)፣ “ማንኛውም ሰው የማሰብ፣…ነፃነት አለው” (አ 27/1) “ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሀሳቡን የመግለጽ መብት አለው። ይህ ነፃነት ከሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሁፍ ወይም በህትመት…የማሰራጨት” መብት አለው (አ 29/2)፣ “ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሳሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው” (አ 30/1) ተብሎ ተደንግጓል፡፡ ይሁንና፣ ዛሬ መጠነኛ ለውጥ ቢታይም፣ እነዚህ ህጎች በወረቀት ላይ የሰፈሩ ብቻ ሆነው ቀርተዋል፡፡

“የብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል ከሥራ ላይ የሚውለው፣ ሀ/…በብሔረሰቡ ወይም በሕዝቡ የሕግ አውጭ ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ የድምጽ ድጋፍ ተቀባይነቱ ሲረጋገጥ…” ነው በማለት ሕጉ እንዴት ስራ ላይ ሊውል እንደሚችል የተደነገገ ሲሆን፣ ሌሎች ቅድመ ሁኔታዎችም ተደርድረዋል። (አ 39/ሀ) ይህ አንቀጽ በተለይ

የሚያሳስበውና የሚያስፈራው፣ ብዙ ክልሎችን በበላይነት የሚመራ ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት፣ የኢትዮጵያ ህልውና በመዳፉ ስር መሆኑ ነው።

ከዚህ ሌላ ግን፣ ህገ መንግስቱ ለብሄር/ብበሔረሰቦች መብት እውቅና ቢሰጥም፣ ዛሬ በኢትዮጵያ ምድር ለሚታየው ግጭትና አለመረጋጋት አንዱ መንስዔ ይኸው በእኩልነት ጥያቄ ላይ የሚታየው ልዩነት ነው። ህወሃት የበላይ በሆነበት ወቅት ትግርኛ ተናጋሪው ቁልፍ የሆኑ መንግስታዊ የኃላፊነትና ሌሎች ቦታዎችን ይዞ የቆየ ሲሆን፣ ዛሬ ያ አሰራር ለተረኛው ተለቋል፡፡ ነገም ሌላ ይመጣል፡፡

## ብሄረተኝነትና ዲሞክራሲ

በወገኖች መሀል ፍቅርንና መተሳሰብን ለመዝራት፣ እናም ለሀገር ግንባታም ሆነ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ለማበርከት፣ ሁሉን አቀፍ አመለካከትን መጎናጸፍ ይጠይቃል፡፡ ያለአድልኦ በእኩልነት ሊዳኝና ሊያስተናግድ የሚችል፣ አርቆ አሳቢ አመራርን ይሻል፡፡ ብሄረተኛነት ላይ የተመሰረተ አሰራር የሚከተል አመራር ሀገርን በአንድነት ይዞ ለመዝለቅ ያዳግተዋል፡፡ የህወሃት አሰራር የቅርብ ጊዜ ትውስታችንና ልምዳችን ነው፡፡

ብሄረተኝነት በዘር ላይ በተመሰረተ የጠላትና ወዳጅ ፍረጃና አካሄድ ላይ የተንተራሰ በመሆኑ አግላይ እንጅ አቃፊ አይደለም፡፡ ባላንጣውና በዳዩ አጠገቡ ቢኖርም ጠላቱ ከእሱ ውጭ ያለው ሌላው ወገን ነው፡፡ ለድህነቱ አጠገቡ ያለው አካል ወይም ቡድን ቢሆንም፣ እንደእሱ መናጢ ደሀ የሆነው ወገንን ጠላት፣ በህይወት ተያይቶ እንኳን የማያውቀው ከእሱ በብዙ ኪሎሜትሮች ርቀት ላይ ያለው ወገንንም ጠላት ብሎ ይፈርጃል፡፡ ዘር ማንዝሮቹ የፖለቲካ ሥልጣን አካባቢ ድርሽ ብሎ የማያውቀው ወገንንም ጠላት ብሎ ይፈርጃል፡፡

ታሪክን ስንፈትሽ፣ የኢትዮጵያ ታሪክም በዓለም ዙሪያ እንዳሉ እንደማንኛቸውም ሀገሮች ነው፡፡ የትኛውም ሀገር ዲሞክራሲን መሰረት አድርጎ አልተመሰረተም፡ ፡ ዲሞክራሲ በግሪክ ውስጥ በጥንት ዘመን ተፈለሰፈ ቢባልም፣ የአገዛዝ አንድ አካል ሆነ ስራ ላይ መዋል የጀመረው በ18ኛው ክፍለ ዘመን ከተካሄደው ከፈረንሳይ አብዮት በኋላ ነው፡፡

ከዚህ ወቅት በፊት በነበረው ጊዜ፣ ሀገሮች ሁሉ የተገነቡት ህይወት ገብረውና ደም አፍስሰው ነው፡፡ አሜሪካ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ አሜሪካዊ ህንዶችን

አጥፍታ፣ ማለትም የዘር ፍጅት ፈጽማ ነው የተገነባችው፡፡ እንግሊዝ ጉልበቷን ያፈረጠመችው በዓለም ዙሪያ በርካታ ቅኝ ሀገሮችን ይዛ፣ ሕዝብ ፈጅታ፣ በዝብዝና ዘርፋ ነው፡፡ ሌሎቹም እንደዚሁ፡፡ የኢትዮጵያ ታሪክም የተለየ አይደለም፡፡ ዛሬ ኢትዮጵያ በምንላት ምድር ብዙ ጦርነቶች ተካሂደዋል፣ ደም ፈሷል፣ አጥንት ተከስክሷል፡፡ አንዱ ከሌላው ጋር ሲዋጋ፣ ሲያሸንፍ፣ ሲሸነፍ ቆይቷል፡፡ ትናንት አንዱ ነገ ደግሞ ሌላው ሲያሸንፍ ሕዝቡን አስገብሯል፡፡ በጉልበት ገዝቷል፡፡ በዚህ የታሪክ ሂደት አንደኛው ወገን የበላይ ሆኖ በመውጣት የኢትዮጵያን ለብዙ ዘመን ገዝቷል፡፡ በዚህ የአገዛዝ ሂደት በርካታ የእድገትና የልማት፣ ሀገርን ከባዕዳን የመከላከልና በነፃነት የማቆየት ተጋድሎ ተካሂዷል፡፡ በአንፃሩ፣ ከአስተዳደር ደካማነት በመነጨ፣ ስህተቶች፣ ወንጀሎች፣ ግፎች፣ አድልኦዎች፣ ወዘተ ተፈጽመዋል፡፡ ያን መካድ አይቻልም፡፡

የያ ትውልድ አባላት የእኩልነት ጥያቄ ምላሽ እንዲያገኝ አምርረው የታገሉት በታሪክ የተፈጸሙ ስህተቶችን ለማረም ነው፡፡ ቂም በቀል ከኢትዮጵያውያን ህሊና ተፍቆ እንዲጠፋ ለመርዳት ነው፡፡ ስህተቶቹ ላይ ተመስርቶ ለብቀላ መዘጋጀት ሳይሆን በአዲስ አስተሳሰብ ወደፊት ለመራመድ እንዲቻል ነው፡፡ ይህን የመሰለ ፖሊሲ ይዞ በመነሳቱ ነው እገሌ ከእገሌ ሳይባል ኢህአፓ በመላ ሀገሪቱ የሚገኙ የተለያየ ቋንቋ ተናጋሪዎችን በአንድ ጥላ ስር ሊያሰልፍ የቻለው፡፡

ለዚህ ሁሉ ነው አሳታፊና አቃፊ የሆነው ዲሞክራሲ አማራጭ የሌለው መፍትሄ የሚሆነው፡፡ ዲሞክራሲ አግላይ የሆነውን የብሄረተኛነት ፖሊሲ ይፃረራል፡፡ ዲሞክራሲ፣ የብሄረተኛነት መሰረት የሆነው የቂም በቀል አሰራርና አመለካከትን አያስተናግድም፡፡ ዲሞክራሲ የብሄረተኛነት መለያ የሆነው የተረኛነት ፖሊሲ ላይ ያልተመሰረተ አካሄድ ነው፡፡ ብሄረተኛነትና ዲሞክራሲ ሆድና ጀርባ ናቸው፡፡ አብረው አይሄዱም፡፡ ስለሆነም፣ ቢያንስ በህገ መንግስትም ሆነ በሀገር ደረጃ የብሄረተኝነት ፖሊሲ ተወግዶ ዲሞክራሲ ቦታውን መያዝ አለበት፡፡

## በዘር መደራጀትና ዲሞክራሲ

በዓለም ዙርያ በዘር መደራጀት በሰው ልጅ ላይ እጅግ የከፋ መከራ አድርሷል፡፡ በዘር ላይ ተመስርቶ ወደ አንድ ሚልዮን ሕዝብ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ የተፈጁበትን ሩዋንዳን ማስታወስ ይበቃል፡፡ በኢትዮጵያም፣ በተለይም

በኦሮምያ፣ በቤኒሻንጉል፣ ወዘተ፣ በተወሰኑ ወረዳዎች በአማራው ላይ የተካሄደውን የዘር ፍጅት ማጤን ይቻላል፡፡

ብሄረተኝነት ተጨባጭ መነሻ ቢኖረውም፣ በአመዛኙ ስሜት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የብሄረተኛ ኃይሉን የሚመራው አካል የፖለቲካ አካሄድ፣ እምነትና የመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ ይመሰረታል፡፡ እናም፣ ብሄረተኝነት ልጓሙን ሲስትና ሲለቅ የማታ ማታ በዘር ፍጅት ሂደት ውስጥ ሊሰማራ ይችላል፡፡

ስለሆነም፣ ዲሞክራሲ ብብሄረተኝነት ላይ የበላይ ሊሆን የሚችለው የአግላይ ፖለቲካ መሰረት ሲነቀል ብቻ ነው፡፡

ዲሞክራሲ ብብሄረተኝነት ላይ የበላይ ሊሆን የሚችለው ለቂም በቀል ፖለቲካ መቆፍቆፍያ የሆነ አሰራርም ሆነ አደረጃጀት ሲወገድ ብቻ ነው፡፡

ዲሞክራሲ ብብሄረተኝነት ላይ የበላይ ሊሆን የሚችለው ከፍቅር ይልቅ በጥላቻ ላይ የተመሰረተ አሰራርና ፖለቲካ ማስተናገድ ሲቆም ነው፡፡

ዲሞክራሲ ብብሄረተኝነት ላይ የበላይ ሊሆን የሚችለው ከአቃፊ ፖለቲካና አሰራር ይልቅ አግላይ አሰራርና ፖለቲካ ቦታውን ሲለቅ ነው፡፡

**ዲሞክራሲ ብብሄረተኝነት ላይ የበላይ ሊሆን የሚችለው ለፖለቲካ ሥልጣን ለሚደረግ ትግል በዘር መደራጀት በህግ ሲከለከል ነው፡፡ ለፖለቲካ ሥልጣን በዘር መደራጀት ከኢትዮጵያ ህገ መንግስት ተፍቆ በአስተሳሰብ፣ በተጠቃሚነትና በጋራ ማንነት ላይ የተመሰረተ አሰራርና አካሄድ መከተል ሲቻል ነው፡፡**

በማሳያነት፣ ኦሮሞዎች፣ አማሮች፣ ጉራጌዎች፣ ወዘተ የሚኖሩበት ክልል ኦሮሞዎች ብቻ በሚሳተፉበት በኦሮሞ ብልጽግና ፓርቲ ብቻ ሳይሆን በኦሮምያ ውስጥ የሚኖሩና በፓርቲው ለመሳተፍና ለመታቀፍ የሚፈልጉ የሌላ ብሄረሰብ አባላት በእኩልነት ሊሳተፉበት የሚችሉበት ድርጅት ሲሆን ነው፡፡ በኦሮምያ የሚኖሩ ሌላ ማንነት ያላቸው ወገኖች ድምጻቸውን ለማሰማት የሚችሉበት መድረክ ሲፈጠር ነው፡፡

ያ ድርጅትም መርሃ ግብሩን ከመቀየር አንስቶ ስሙንም ሊለውጥ ይችላል፡፡ በተጨማሪ፣ ድርጅቱ፣ በኦሮምያ በመከለል ፈንታ አማራ፣ ሶማሊያ፣ ደቡብ፣ ወዘተ ክልሎች ውስጥ የሚገኙ አባላትን ሊመለምል ይችላል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስቴር ዓብይ በመጀመሪያ ደረጃ፣ ሰው፣ ቀጥሎም ኢትዮጵያዊ፣ ከዚያም ኦሮሞ ናቸውና፣ በዘር የተደራጀ ፓርቲ መሪ ሳይሆን ኢትዮጵያን የሚመጥን የፖለቲካ ድርጅት መሪ ነው መሆን ያለባቸው፡፡ ወደዱም ጠሉ፣ በዘር ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ ድርጅት መሪነታቸው፣ እንደ ኦሮሞ እንዲያስቡና እንዲንቀሳቀሱ ተጽእኖ ያሳድርባቸዋል፡፡ እንደ ኢትዮጵያዊ የማሰብ ዕድሉን ያጠብባቸዋል፡፡

ይህ በዘር ላይ የተመሰረተ አሰራር፣ በአማራ ክልልም ተፈጻሚነት ኖሮት፣ ከአማራ ሌላ፣ አገዎች፣ ሽናሻዎች፣ ኦሮሞዎች፣ ወዘተ የሚሳተፉበት ሥርዓት መዘርጋትን ይመለከታል፡፡ ፓርቲው ክልሉን መምሰል ይኖርበታል፡፡ ደግሞም አንድ ፓርቲ ብቻ ሳይሆን የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን የሚወክሉ፣ በአስተሳሰብና በፖሊሲዎች ላይ የተመሰረቱ ፓርቲዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡

**ባህልን፣ ቋንቋን፣ ወዘተ ለመታደግ በማንነት መደራጀቱ ጥቅም ሊኖረው እንደሚችል ግልጽ ሲሆን፣ ኢትዮጵያን ከከፋ ዕልቂትም ሆነ ጥፋት ለማትረፍ፣ ጊዜው ሳይረፍድ በማንነትና በሃይማኖት ላይ ተመስርቶ ለፖለቲካ ሥልጣን መደራጀት በህግ ሊታገድ ይገባል፡፡** መጪው ምርጫ በዚህ ጉዳይ ላይ ትኩረት እንዲያደርግ ከወዲሁ ሰፊ ስራ መሰራት ይኖርበታል፡፡

መደምደሚያ

የኢትዮጵያ ተፎካካሪ ኃይል፣ ህገ መንግስቱ እንዲሻሻል፣ ነገ ሳይሆን ዛሬ፣ ሰፊ ዘመቻና ስራ ማከናወን ይኖርበታል፡፡ ለዚህም፣ 1/ ይህን ሂደት የሚመራ የጋራ አካል በመፍጠር ስራውን መጀመር፣ 2/ ህገ መንግስቱ ላይ የሚሰራ የህግ ባለሙያዎች አካል መፍጠር 3/ ቢቻል በወር አንድ ጊዜ ህገ መንግስታዊ ክርክርና ውይይት ማካሄድ፣ 4/ በሀገር ውስጥ የአየር ሰዓት በመከራየትም ሆነ በሌላ ዘዴ ቋሚ ፕሮግራም እየተዘጋጀ ለሕዝብ ማድረስ ናቸው፡፡ ይህ ስራ የመንግስትን ይሁንታ መጠበቅ አያሻውም፡፡ ጽንፈኛ ብሄረተኛነትን በመታገል የተሻለች ኢትዮጵያን እንፍጠር፡፡ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!